**ሰቆቃ ወጎንደር**
ሙሉቀን ተስፋው



በገፅ 9

**"ዘመን የመጣላት" በርሜ**
መስከረም አበራ



በገፅ 7

**"በብሔረሰቦች መካከል ያለው ግንኙነትና ጥላቻ በጣም የሚረብሽ ነው"**
ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም


በገፅ 5




# የቀለም ቀንድ

ቅጽ 3 ቁጥር 20 ህዳር 28 ቀን 2008ዓ.ም ዋጋው ብር 10.00


# መፈክርና ዘመቻ! 2



## በጎንደር ማረሚያ ቤት በተፈጠረ ግጭት ከ43 በላይ ሰዎች ሞቱ

■ በደብረታቦር የመንግሥት ሚሊሻ የሁለት አርሶ አደሮችን ሕይወት አጥፍቷል

በጎንደር ማረሚያ ቤት ሕዳር 21 እና 23 ቀን ከፖሊስ ጋር በተፈጠረ ግጭት ቢያንስ የ43 ሰዎች ሕይወት አልፏል። ሕዳር 21 ቀን 2008 ዓ.ም. ከቀኑ 7፡00 አካባቢ ማረሚያ ቤቱ ውስጥ ከተነሳ እሳት ለማምለጥ በሞከሩ የሕግ ታራሚዎችና የጥበቃ ፖሊሶች የተጀመረው አለመግባባት አድጎ ለብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል። በፖሊስ ጥይት ከተገደሉት ውስጥ ያልታሰሩ መደበኛ የቀን ሥራቸውን ሲያከናውኑ የነበሩ ንጹሐን ዜጎች ሁሉ ይገኙበታል። የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው የዓይን እማኞች እንደገለጹት ካፍቴሪያ ውስጥ እየተጠቀሙ የነበሩ፣ የባጃጅ ትራስፖርት የሚጠቀሙ፣ ኳስ በመጫዎት ላይ የነበሩ ልጆችና የመኪና ረዳት ሁሉ ተገድለዋል።

ሕዳር 21 ቀን ሕይወታቸውን ያጡ ሰዎች ቁጥር በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎች ነው ያሉት። በጊዜው በአካባቢው የነበሩና ከተጎጅዎች ወገን የነበሩ ሰዎች ሕዳር 21 ቀን ብቻ የተገደሉ የሕግ ታራሚዎች ቁጥር ከ38 ይበልጣል ያሉ ሲሆን ይህ አሃዝ ግን ታራሚ ያልነበሩ ሰዎችን አይጨምርም። በጎንደር ከተማ የሚሠራና ማረሚያ ቤቱን በደንብ አውቀዋለሁ የሚለው የሕግ ባለሙያ ያነጋገራቸውን የሥራ ኃላፊዎች መሠረት አድርጎ የተገደሉ ሰዎች ቁጥር ከ26 በላይ እንደሆነ ተናግሯል። ሕዳር 21 ቀን ከተገደሉ

ወደ ገፅ 3 ዞሯል

## በኦሮሚያ የተለያዩ ከተሞች ተቃውሞው ቀጥሏል

■ ኦፌኮ የአዲስ አበባና የኦሮሚያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላንን እንደማይቀበል ገለጸ

በገፅ 3

## በድርቅ የተጎዱ አካባቢዎች የውኃ እጥረት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል

በገፅ 3

## ርእስ አንቀፅ

# መፈክርና ዘመቻ የተረሳው የረኀብተኞች ጬኸት !

በድርቁ ምክንያት የተጎዱና የተራቡ ዜጎች በሚያሳዝን ሁኔታ ተረስተዋል! ድርቅ እንደሚከሰት እና ችግሩ ለረዥም ጊዜ ሊቆይ እንደሚችል በሚገባ እየታወቀ አገዛዙ ሥልጣኑን በማደላደል ላይ፤ ከመቶ በመቶ ‹‹አሸናፊነቱ›› በኋላ ደግሞ በአሸሸ ገዳሜና በዳንኪራ ተጠምዶ ምንም ዓይነት ዝግጅት ሳያደርግ ቆይቷል፡፡ ‹‹ድርቁ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ነው፤ ዜጎች እየተጉዱ ነው›› የሚሉትን ማሳሰቢያዎች አገዛዙ ሲያጣጥላቸው እንደቆየም የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡ የቀድሞው የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ሚኒስትር አቶ ሬዲዋን ሁሴን ‹‹መንግሥት በድርቁ ምክንያት የተጎዱ ዜጎችን ቁጥር የሚመግብ በቂ ክምችት አለው፤ ጉዳዩ ከመንግሥት ቁጥጥር ውጪ አይደለም›› ብለው በመኩራራት ስሜት ሲነግሩን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደግሞ በሚያስተዛዝብ ሁኔታ በኢሕአዴጋውያን በተሞላው ፓርላማ ፊት ቀርበው ‹‹ችግሩ ሰፊና ለረዥም ጊዜ የቀየ ቢሆንም የሠራናቸው ጠንካራ የአፈር ጥበቃና የውኃ ማቆር/መያዝ ሥራዎች ችግሩ በሰው ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ረድተውናል፤ የተወሰኑ እንስሳት ቢሞቱም ኅብረተሰቡ ባለው የተለመደ የመደጋገፍ ባህል መሠረት ከብት ያላቸው ወገኖች ለሞተባቸው ወገኖች እየሰጡ ችግሩን እየተቋቋሙት ነው›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡

መንግሥት በድርቁ የተጎዱ ወገኖችን ቁጥር የሚደብቅበት ምንም ምክንያት የለም ቢባልም የተጎጂዎች ቁጥር በጣም አንሶ ሲዘገብና ሪፖርት ሲቀርብ መቆየቱ በሒደት ተረጋግጧል፡፡ የመንግሥት ባለሥልጣናት በድርቁ የተጎዱት ዜጎች ውስሱን በመሆኑ ችግሩ ከመንግሥት ቁጥጥር ውጪ አይደለም ባሉበት አንደበታቸው የለጋሽ ድርጅቶችን ድጋፍና እርዳታ ሲማጸኑም ታዝበናል፡፡ ቅጥፈቱ የተጎጂዎችን ቁጥር በማሳነስ ብቻ አልተገታም፡፡ ችግሩ ወደ ረኀብነት ተቀይሮ በረኀብ ምክንያት የሞቱ ዜጎች ስለመኖራቸው ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን በሚዘግቡበት ወቅት ‹‹ረኀብ የለም፤ በረኀብ የሞተ አንድ ሰውም የለም፤ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ችግሩን እያጋነኑ የሚያራግቡት ድጋፍ ለማግኘት እንዲያመቻቸው ነው›› ወዘተ. ሲባልና በሚያስተዛዝብና በሚያሳፍር ሁኔታ የተጎዱ ዜጎች አልተጎዳንም እንዲሉ ሲገደዱም ታዝበናል፡፡

ይሁን እንጂ ያፈጠጠውን እውነታ የአገዛዙ መገናኛ ብዙሃን የነተበ የዘገባ ጋጋታና የባለሥልጣናቱ መግለጫ ሊደብቀው አልቻለም፡፡ አገዛዙ ጉዳዩን ረስቶት ከከረመ በኋላ ችግሩ ሊደበቅ የማይችል መሆኑ ሲታወቅ ደግሞ ሌላ መዝሙር እየሰማን ነው፡፡ ረኀብና ችጋር ጊዜ የማይሰጥ አፋጣኝ ምልሽና ርብርቦሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ሳለ፣ የቅድሚያ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን ጉዳይ ወደ ጎን በመግፋት ‹‹እንደዚህ ያለ ድርቅ በአገራችን ታሪክ ታይቶ አይታወቅም፤ ኢሕአዴግ የሚመራው መንግሥት ባይኖር ኖሮ እጅግ ብዙ ሕዝብ ሊያልቅ ይችል ነበር›› የሚል ሰንካላ ሐተታ ሲቀርብ እየታዘብን ነው፡፡ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በረኀብ ምክንያት የሚሞቱና አካባቢያቸውን ጥለው የሚሰደዱ ዜጎችን በመደገፉ ላይ እንዲረባረብ ጥሪ ከማድረግ ይልቅ ድርቁን እንደፖለቲካ መሣሪያ ለመጠቀም፤ እኛ ባንኖር ችግሩ ሕዝብ ይጨርስ ነበር እያሉ ርካሽ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ ለመሥራት መሞከር በሕዝብ ሕይወት ላይ መቀለድ ከመሆኑ ሌላ በሕግም በታሪክም የሚያስጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡

መቼም ኢሕአዴግ እንደ ባሕርይ ወንድሙ እንደ ደርግ መፈክርና ዘመቻ ይወዳል! የሚገርመው የሁለቱም መፈክርና ዘመቻ የእምቧይ ካብ ሲሆን ነው የሚታየው፡፡ ‹‹ኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያን እንመሠርታለን!››፣ ‹‹ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ሥር እናውላለን!›› ወዘተ. ሲባል ከርሞ የሆነውን ሁሉ የምናውቀው ነው፡፡ በዘመነ ኢሕአዴግም ‹‹ሚሊዮን ሚሊየነር አርሶ አደሮችን የፈጠረውን ምርጥ ተመክሯችን እናስፋለን!››፣ ‹‹መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን ዕውን በማድረግ የታላቁን መሪ ርዕይ እናሳካለን!፣ የብሔር ብሔረሰቦች መብት መከበር የልማታችን ምስጢር ነው!›› ወዘተ. ሲባል የከረመ ቢሆንም እንኳን ልማት ሊታይ፣ እንኳን ሚሊዮን ሚሊየነር አርሶ አደር ሊፈጠር ሕዝባችን የአንድ ወቅት የዝናብ እጥረትንም መቋቋም እንዳልቻለ በገሃድ እየታየ ነው፡፡ በእርግጥ ከአገዛዙ ጋር ተጠጋግተው በአንድ ጀንበር የከበሩ ኃይሎች አሉ፡፡ ትርፍ አምራች የሆኑ አካባቢዎች አሁንም ትርፍ እያመረቱ ነው እየተባለ የሚነገረው ግን እንዲያው ከንቱ ጬኸት ብቻ ነው፡፡ ትርፍ ከተመረተ ለምን ወደተጎዱት አካባቢዎች እንዲደርስ አይደረግም?

ሐቁን እንጋፈጠው፡፡ ሐቁ የኢትዮጵያ አርሶ አደር አሁን ባለው የመሬት ይዞታው ራሱን ሊመግብ የሚችልበት ዕድል የመነመነና በአንድ ወቅት የግብርና ሚኒስትሩ በግልጽ እንደተናገሩት የተዘጋ አማራጭ መሆኑ ነው፡፡ ችግሩ የድርቁ ከባድነት ሳይሆን ድርቅ በመጣ ቁጥር ዜጎች የሚራቡት በፖሊሲ ችግር ምክንያት መሆኑ ነው፡፡ ግልጽ የፖሊሲና የሥርዓት ችግር መሆኑ የሚያከራክር አይደልም፡፡ ዓለምን ያስደመመ፣ በአፍሪካ ቀዳሚና ምሳሌ የሆነ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ አለን ሲባል የከረመው የወሬ ጋጋታ ሁሉ ባዶ ጬኸትና መፈክር ብቻ ነው፡፡

## ትዝብት

ሩት አማኑኤል

# "ሒደት ነው"

ተደጋግሞ የሚነገር አንድ ጉዳይ አለ፡፡ ዴሞክራሲ ሒደት ነው፤ መልካም አስተዳደር በሒደት የሚመጣ ነገር ነው፤ የዴሞክራሲ ተቋማትን መገንባት ሒደት ነው ወዘተ. ይባላል፡፡ ለጽሑፌ መነሻ የሆነኝ የጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ንግግር ነው፡፡ አቶ ኃይለማርያም ከሪፖርተር ጋዜጣ ጋር (እሑድ ኅዳር 19 ቀን 2008 ዓ.ም.) ባደረጉት ቃለምልልስ ስለመልካም አስተዳደር ተጠይቀው ሲመልሱ ‹‹… የመልካም አስተዳደር ችግር በሒደት እየተገነባ የሚሄድና አፈታቱም ቢሆን ኅብረተሰቡ ራሱ ተሳትፎበትና ባለቤት ሆኖበት የሚፈታ ጉዳይ እንጂ፣ የመንግሥት ባለሥልጣናት ስለተሰበሰቡ ብቻ የሚፈታ ተደርጎ መውሰድ የለበትም፡፡›› ብለው ነበር፡፡

ይታያችሁ፣ ኢሕአዴግ ከአጼ ኃይለሥላሴ አገዛዝ ቀጥሎ ለረዥም ጊዜ አገሪቱን የገዛና አሁንም በሥልጣን ላይ ያለ አገዛዝ ቢሆንም ባለፉት ሃያ አራት ዓመታት ውስጥ የዴሞክራሲ ጭላንጭል እየሰፋና እያበበ ከመሄድ ይልቅ እድገቱ ቁልቁል ሆኖ ሳለ ስለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሒደትነት ሲነገረን፡፡ አዎ፣ ዴሞክራሲ ሒደት ነው፡፡ ሒደት ነው ማለት ግን ተጀምሮ በየጊዜው እያደገና እየጠነከረ ይሄዳል ማለት ነው እንጂ እንደ ዘመነ ኢሕአዴግ ዴሞክራሲ አድሮ ቃሪያ ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ አዎ፣ የዴሞክራሲ ተቋማትን መገንባትና ማጠናከር ሒደት ነው፤ ጊዜ ይጠይቃል፡፡ ሒደት ነው ማለት ግን መንግሥታዊ ተቋማት የአገዛዙ የመጋለቢያ መሣሪያዎች ይሆናሉ፣ አገዛዙ ተቀናቃኞቹን ለማኮላሸት የሚጠቀምባቸው የአፈና መሣሪያዎች ይሆናሉ ማለት አይደለም፡፡ አዎ፣ መልካም አስተዳደርን ማስፈን ሒደት ነው፡፡ ሒደት ነው ማለት ግን እስኪበቃን እንዳየነው የአምባገነኑ ሥርዓት ባለሥልጣናትና ተላላኪዎች የሳምንት ወይም የወር የዘመቻ ሥራ ነው ማለት አይደልም፡፡

አምባገነኖች ስለ ሒደት ማውራት ይወዳሉ፡፡ ኢሕአዴም እንደ አንድ አምባገነን ድርጅት ይህንኑ ጉዳይ መልሶ መላልሶ ሲወቅጠው እየተዛብን ነው፡፡ ‹‹ከጸረ ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ የተላቀቅነው በቅርቡ ነው፤ የጸረ ዴሞክራሲያዊ አገዛዙን ቅሪት አስወግዶ ዴሞክራሲን መገንባት ከባድ ነው፤ እኛ ግን ከመጀመሪያው ጀምረን ዴሞክራሲ የህልውና ጉዳይ ነው ብለን ስለምናምን ሒደቱን ጀምረናዋል፤ ይሁን እንጂ ዴሞክራሲ ሒደት የሚጠይቅ ነገር በመሆኑ የጀመርነው ዴሞክራሲ አሁንም ጮርቃ ነው፤ ለጋ ነው፤ ስለዚህ ቀጣይ ሥራችን ይህን የጀመርነውን ዴሞክራሲ የትምክህትና የጥበት ኃይሎች እንዳያኮላሹትና አገራችንን ለብተናና ትርምስ እንዳይዳርጓት እነሱን እየታገልን መቀጠል ነው፡፡›› ይባላል፤ ይደጋገማል - በአገዛዙ በኩል፡፡

ይሁን እንጂ ደግሞ አገዛዙ በሙስናና በዘረፋ እስከ አንገቱ የተዘፈቀ ነውና ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲፈጠር ጨርሶ እንደማይፈልግ በጣም ግልጽ ነው፡፡ የእስካሁኑ ድርጊቱ የሚመሰክረውም ይህንኑ ሐቅ ነው፡፡ ዜጎች ደልቷቸው ጉቦ ይሰጡ ይመስል አቶ ኃይለማርያም ለባህር ዳር ከተማ ነዋሪዎች ‹‹ቢያንስ ጉቦ አትስጡ፤ ጉቦ የሚሰጥ ከሌለ ተቀባይም አይኖርም›› የሚል ከንቱ አስተያየት መስጠታቸውን አስመልክቼ ባለፈው ሳምንት ጽሑፌ አንዳንድ ነገሮችን አንስቼ ነበር፡፡ እኚህ ሰውየ አሁን ደግሞ መልካም አስተዳደርን ስለማስፈን ሒደትነት ሊያስተምሩን በከንቱ ሲባክኑ እያየን ነው፡፡ ሒደትነቱ መቼ ጠፋን፡፡ የኛ መነሻ ሒደቱ አልተጀመረም ብቻ ሳይሆን የመልካም አስተዳደር ችግሩ ምንጭ አገዛዙ ራሱ በመሆኑ ከቶም ሊጀምረው አይችልም የሚለው ነው፡፡ የኛ መከራከሪያ አገዛዙ የፖለቲካ መሠረት ጥቅም ነውና መሠረቱን የሚንድ ሥራ አይሠራም፤ የሚባለው ሁሉ ማስመሰል ነው የሚለው ነው፡፡ ግልጽ ነው?

በዲኦንሔር ፐብሊሺንግ ሚዲያ እና ኮምኒኬሽን ኃላ.የተ.የግ. ማኅበር እየተዘጋጀ የሚቀርብ ሳምንታዊ ጋዜጣ

**ሥራ አስኪያጅ**
አበበ ውቤ

**ዋና አዘጋጅ**
ሙሉቀን ተሰፋው
0910159783
mulukentesfaw@gmail.com
የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 09/297


**ሪፖርተር**
ትሑት ጥላሁን

**አምደኞች**
መስከረም አበራ
ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)
ሩት አማኑኤል
መብራቱ በላቸው
በሪሁን አዳነ
ታዲዮስ ታንቱ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 08
ቤ/ቁጥር 471
ስልክ፡ 0910159783
0919396240

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ስልክ፤ 0911 18 09 33

**አታሚ**
‹‹ሶፍ ሚክ ማታሚያ ቤት
ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 04
የቤት ቁጥር 64



# ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም የብሔረሰብ ጥላቻው አደገኛ ደረጃ ላይ ደርሷል ሲሉ አስጠነቀቁ

ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም በብሔረሰቦች መካከል እየተፈጠረ ያለው ጥላቻ አደገኛ ሁኔታ ላይ ደርሷል ሲል አስጠነቀቁ:: ከዚህ በፊት በሠራሁባቸው አገሮች ያየሁት ነገር በአገሬ እንዲከሰት ፈጽሞ አልፈልግም የሚሉት ዶ/ር ያዕቆብ፣ ችግሩ በተከሰተባቸው አገሮች እንደሳቸው ያሉ ሰዎች አስቀድመው ቢያስጠነቅቁም የሚሰማቸው ባለመገኘቱ እጅግ አስከፊ ሁኔታ መፈጠሩን በመጥቀስ በአገራችንም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ሁሉም ዜጋ በተለይም አገር ሽማግሌዎች ከፍተኛ ጥረት ሊያደርጉ ይገባል ብለዋል::

ዶ/ር ያዕቆብ እንዳብራሩት በአገራችን ግለሰቦች በየምክንያቱ ከሚደርስባቸው የዘር ወይም የብሔረሰብ ጥላቻ አልፎ በሶሻል ሚዲያዎች የሚጻፈውን ጸያፍ ስድብና ጥላቻ ለተገነዘበው እንቅልፍ የሚነሳ ጉዳይ ነው፤ የዚህ ዓይነቱን ጥላቻ የሚያንጸባርቁት ጥቂቶች ናቸው ብሎ በለሆሳስ መተው አይቻልም:: እንደዚህ ዓይነቱን ጥላቻ ለማጥፋት መፍትሔው ሰውን አስሮ መቀጥቀጥ አይደለም ወይንም አውሎ ንፋስ መምጣቱን እያየች የለም ብላ ራሷን አሸዋ ውስጥ እንደቀበረችው ሰጎን መሆን አይደለም:: እነዚህ የብሔረሰብ ጥላቻ የተጠናወታቸው ሰዎች አቋማቸው ስህተት ቢሆንም ለራሳቸው በቂ ምክንያት አላቸው::

ለዚህ ሁሉ መፍትሔው ብሔራዊ እርቅ ነው ያሉት ዶ/ር ያዕቆብ አያይዘውም ፐ/ር መስፍን ወልደማርያም፣ ልዑል ራስ ስዩምና አቶ ሽመልስ አዱኛን የመሳሰሉ የአገር ሽማግሌዎች ዝም ማለት የለባቸውም ሲሉ አሳስበዋል:: የአገር ሽማግሌዎች ከምንጊዜውም በላይ አሁን ስለአገር አንድነትና ደህንነት ሊጨነቁና መላ ሊመቱ ይገባል ሲሉ የሕግ ምሁሩ አክለው ገልጸዋል::


# በድርቅ የተጎዱ አካባቢዎች የውኃ እጥረት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል

በድርቁ የተጎዱ የወሎና ከፊል የጎንደር አካባቢዎች የውኃ ችግር አሳሳቢ መሆኑን ነው የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው ሰዎች የገለጹልን:: ከዋግኽምራና ከምሥራቅ በለሳ አካባቢ እንደመጡ የሚናገሩ አዲስ ዘመን ከተማ ያገኘናቸው አካባቢያቸውን ለቀው የሚሰደዱ ሰዎች እንደሚሉት ድርቁ ያስከተለው ጉዳት መግለጽ ከምንችለው በላይ ነው ብለዋል:: እብናት ከተማ በርካታ ስደተኞች እንዳሉ የሚናገሩት እነዚሁ ሰዎች ነዋሪው በጅምላ አካባቢውን ለቆ በመሰደድ ላይ እንደሆነ ነው የገለጹት:: እርዳታ አሰጣጡም ላይ የድርጅታዊ አባልነት መድሎ እንዳለበት ሁሉ ተናግረዋል:: የመሬት ግብር ክፈሉ የሚባሉ አካባቢዎች እንዳሉ ነው የሚናገሩት:: እብናት ላይ ምነ ያክል ሰው አካባቢውን ለቆ እንደመጣ እንዲነግሩን ላቀረብንላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ‹‹ትንሽ ቀን ከዚህ ከሰነበትክ ቶሎ እዚህ ስለሚደርሱ ታየዋለህ›› ሲሉ በጅምላ የሚሰደዱ ሰዎችን ብዛት ገልጸዋል::

በተያያዘ ዜና በደቡብ ጎንደር በታች ጋይንትና በስማዳ ቆላማ አካባቢዎች የድርቁ ሁኔታ በርካታ እንስሳትን ሕይወት ቀጥፏል ያሉን በባህር ዳርና ወረታ አካባቢዎች ያገኘናቸው ግለሰቦች ናቸው:: እነዚሁ የአይን ምስክሮች እንደሚሉት በስማዳ የውኃ ጥምን ለማርካት ከብቶች ሲታረዱ ከፈርሱና መሰል ነገሮች የሚወጣውን ቆሻሻ ፈሳሽ እስከመጠጣት የደረሱ ሰዎች አሉ ብለዋል:: በመንግሥት በኩል ነጋዴዎች ገብተው በድርቁ ምክንያት ሊሞቱ የሚችሉትን እንስሳት እንዲገዙ ቢደረግም ነጋዴዎቹ የእንስሳቱን ዋጋ እንዲረክስ አድርገዋል ብለዋል:: በየቀኑ የሚታየውና የሚሆነው ሰቅጣጭ እንደሆነ የሚናገሩት ተጎጅዎች ራቅ ባሉት የስማዳና የታች ጋይንት አካባቢዎች የመኪና መንገድ ባለመኖሩ የእርዳታ እህሉ በአህያ ጭነት እንዲጓጓዝ ቢደረግም በበቂ ሁኔታ ሊቀርብ አልቻለም ተብሏል:: የውኃ ችግሩን ለማቃለልና የማጓጓዣ ትራንስፖርቱን ለማቃለል ነዋሪዎች ተነስተው የተሻለ የውኃና የመሠረተ ልማት አቅርቦት ወዳለበት ቦታ መቅረብ ግድ እንደሚላቸው ነው ብዙዎች የሚናገሩት::

እንደአስተያየት ሰጭዎቹ በእርዳታ የሚመጣው እህል ሙሉ በሙሉ ወደተጠቃሚዎች እየደረሰ እንዳልሆነም ነው የሚናገሩት:: ዜጎች እንደዚህ በረኃብና በውኃ ጥም እንዲህ እያለቁ ባለበት በአሁኑ ሰዓት ለእርዳታ የሚመጣው እህል በአግባቡ እንዱከፋፈል መንግሥት ትኩረት እንዲሰጥም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል::

# በጎንደር ማረሚያ ቤት . . .



ሰዎች ውስጥ ወደ ሆስፒታል የተወሰደ አስከሬን 17 መሆኑን ለማወቅ ተችሏል:: አንድ ስሙ እንዳይጠቀስ የፈለገ የፖሊስ አባል በበኩሉ 22 ሰዎች መገደላቸውን እንደሚያውቅ ተናግሯል:: ሕዳር 21 ቀን ከተገደሉ ሰዎች ውስጥ ዘመድ አዝማድ ያልተገኘላቸውና አስከሬናቸው በሪፈራል ሆስፒታሉ አስከሬን ክፍል እንደሚገኝም ታውቋል:: የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሪፈራል ሆስፒታል ሕዳር 22 ቀን የተወሰኑ ክፍሎች ዝግ ሆነው በፖሊስ የሚጠበቁ የነበረ ሲሆን በቀጣዩ ቀን ከገቡ በኋላ የሞቱ የሁለት ሰዎችን ዝርዝርም በማስታወቂያ ገልጧል::

የዞኑ ማረሚያ ቤት መምሪያ የጎንደር ማረሚያ ቤትን በድንገት ባእታ አካባቢ ካለው አዲስ ወደተሠራው አንገረብ ማረሚያ ቤት ሕዳር 22 ቀን ያዛወረ ቢሆንም ውኃና ምግብ የተሟላ አይደለም በሚል እንዲሁም በዘመድ አዝማዶቻችን እንጠየቅ የሚል ውዝግብ ሕዳር 23 ቀን እንደተነሳ በቦታው ተገኝቶ ዝግጅት ክፍላችን አረጋግጧል:: ከማረሚያ ቤቱ ውስጥ የእሳር ቃጠሎ ከ5፡00 ጀምሮ እስከ 7፡00 አካባቢ የተስተዋለ ሲሆን በማኅበረሰቡና በፖሊስ መካከልም ግጭት ተከስቶ ነበር:: ሕዳር 23 ቀን በተፈጠረው ዳግም ግጭት በጥይት ሕይወታቸው ያጡ 21 ሰዎች አስከሬን ወደ ሆስፒታል መወሰዱን ለማወቅ ተችሏል:: ሆኖም በዚሁ ቀን የተገደሉትን በተመለከተ ከማረሚያ ቤቱ የተሰጠ ይፋ መግለጫ የለም:: ይህ በዚህ እንዳለ ከግጭቱ ጋር በተያያዘ የማረሚያ ቤቱ ኃላፊ መታሰሩም ታውቋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሕዳር 23 ቀን 2008 ዓ.ም. በደቡብ ጎንደር ደብረ ታቦር ከተማ አንድ የመንግሥት ሚሊሻ ከገጠር የመጡ ሁለት ገበሬዎችን የገደለ ሲሆን ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ቀን ድረስም በቁጥጥር ሥር እንዳልዋለ ታውቋል:: ሁለቱ ሟች ገበሬዎች የፋርጣ ወረዳ ሊማዶ ቀበሌ ነዋሪዎች እንደነበሩም ለዝግጅት ክፍላችን መረጃውን የሰጡ አካላት ገልጸዋል::

# በኦሮሚያ የተለያዩ ከተሞች ተቃውሞው ቀጥሏል

## • ኦፌኮ የአዲስ አበባና የኦሮሚያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላንን እንደማይቀበል ገለጸ

በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች በሚገኙ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተነሳውን ተቃውሞ መሠረት በማድረግ የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረንስ ሕዳር 22 ቀን 2008 ዓ.ም. ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ የአዲስ አበባንና ኦሮሚያን የተቀናጀ ማስተር ፕላን እንደማይቀበል ገልጿል:: ኦፌኮ ባወጣው መግለጫ መልስ ያስፈልጋቸዋል ያላቸውን ዐሥር ጥያቄዎች ያቀረበ ሲሆን እነዚህ ጥያቄዎች ካልተመለሱ ግን ‹‹በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር አጠቃላይ ሰለማዊ ሰልፍና ማናቸውንም የሰላማዊ ትግል ስልት ለመተግበር እንገደዳለን›› ሲል አስጠንቅቋል::

የፓርቲው ዋና ጸሐፊ አቶ በቀለ ነጋ ለቀለም ቀንድ ዝግጅት ክፍል እንደገለጹት በምዕራብ ወለጋ ጉልሶና በምሥራቅ ሸዋ ቶሌ አካባቢዎች የሦስት ተማሪዎች ሕይወት አልፏል:: ተቃውሞው በምዕራብ ሸዋ (ጊንጭ፣ አምቦና ባኮ)፣ በምሥራቅ ወለጋ (ነቀምት)፣ በምዕራብ ወለጋ ( ጊምቢ፣ ኔጆ፣ ጉሊሶ፣ አይራ)፣ በቄለም ወለጋ (ደምቢዶሎ)፣ በጉጅ (ሀረቀሎና መልካ ኦዳ)፣ በአርሲ (አቦምሳና ሻሸመኔ)፣ በምሥራቅ ሐረርጌ (ጨለንቆ) እንዲሁም በመቱ፣ በመዳዋላቡ፣ ቡሌ ሆራና ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲዎች ተቃውሞዎች እንደቀጠሉ አቶ ነጋ ገልጸዋል:: ኦፌኮ በመግለጫው በነጆ 114፣ በአምቦ፣ በጊንጪ፣ በወሊሶና በመንዲ ከ1000 በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች እንደታሰሩም ጨምሮ ገልጿል::

በተያያዘ ዜና ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የአንድ ተማሪ ሕይወት እንዳለፈ የሚራገበው ወሬ ከእውነት የራቀ መሆኑን ገልጾ ትምህርታቸውን ያቋረጡ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ ጥሪ ማቅረቡ ታውቋል::

# ጫንጮ ከተማ ውስጥ የሚገኝ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች ራሳቸውን እየሳቱ መውደቃቸው ተገለጸ

በጫንጮ ከተማ በሚገኝ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ከ80 በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ድንገት መውደቃቸው ተገለጸ:: ባለፈው ሳምንት ረቡዕ ተማሪዎቹ በድንገት የወደቁት ምንነቱ ባልታወቀ ምክንያት ሲሆን በተለያዩ ክፍሎች በመማር ላይ የነበሩ ተማሪዎች ድንገት ራሳቸውን እየሳቱ የወደቁ ሲሆን ከ30 በላይ የሚሆኑት ልጆች መንቃት የቻሉት ሕክምና ካገኙ በኋላ ነው ተብሏል::

አንዳንድ ያነጋገርናቸው ነዋሪዎች የችግሩ ምክንያት የመንግሥት የጸጥታ ቡድን አባላት ተቃውሞ ከመነሳቱ በፊት ለመከላከል የረጨት የመርዝ ጋዝ ነው ቢሉም በመንግሥት በኩል እስካሁን ድረስ የተባለ ነገር የለም::

# ታጋይና ደራሲ አስማማው ኃይሉን የሚዘክር መርሐ ግብር ተካሄደ

በቅርቡ ሕይወቱ ያለፈውን የታጋይና ደራሲ አስማማው ኃይሉን (አያ ሻረውን) የሕይወት ታሪክ የሚዘክር መርሐ ግብር በዋቢ ሸበሌ ሆቴል ሕዳር 18 ቀን 2008 ዓ.ም. ተካሄደ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ወታደራዊ ክንፍ ኢሕአሠ ታጋይ የነበረው ታጋይና ደራሲ አስማማው ኃይሉ ለአምስት ዓመታት በኢሕአሠ ታጋይነት ከቆየ በኋላ ለደርጅታዊ ተልዕኮ በሚንቀሳቀስበት ወቅት ተይዞ በደብረ ማርቆስና በጎንደር እስር ቤቶች ታስሮ ቆይቷል:: ከእስር ቤት ከተፈታ በኋላ ወደ ሱዳን አቅንቶ ለተወሰኑ ጊዜያት በዚያው በሱዳን ከቆየ በኋላ በስደተኛነት ወደ አሜሪካ አቅንቷል:: በመርሐ ግብሩ ላይ እንደተወሳው አያ ሻረው በ30 ዓመት የአሜሪካን አገር የስደት ዘመን ቆይታው ከ7 በላይ የታተሙና ያልታተሙ መጽሐፍትን አበርክቷል::

በመርሐ ግብሩ ላይ አርቲስት ተፈሪ ዓለሙ፣ አቶ በኃይሉ ገብረእግዚአብሔር፣ ገጣሚ ደምሰው መርሻና ባንቺ ዓለሙ ከደራሲው ሥራዎች ውስጥ ለታዳሚዎች ያነበቡ ሲሆን ደራሲና ሐያሲ ዓለማየሁ ገላጋይ የአስማማው ኃይሉን የድርሰት ሕይወት ዳሰሳ አቅርቧል:: የአያ ሻረው አንድ ሥራ በቅርቡ እንደሚታተምም በመርሐ ግብሩ ላይ ተጠቁሟል::

ወቅታዊ

# ብሔራዊ መግባባት ከወዴት አለሽ !

ገዥው ግንባርና ዋና ዋና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ከሚስማሙባቸው ጥቂት አጀንዳዎች መካከል ፌዴራሊዝም አንዱ ነው፡፡ በቅርጹ ላይ ያላቸው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ብዙሃኑ ኃይሎች ለኢትዮጵያ የሚበጀው ፌዴራሊዝም እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ ብዙዎችም በፕሮግራማቸው ሳይቀር ስለፌዴራል ሥርዓት አስፈላጊነት ይገልጻሉ፡፡ ኢትዮጵያ ኅብረ-ብሔር እና ኅብረ-ኃይማኖት የሆነች አገር በመሆኗ የተሻለው የመንግሥት አወቃቀር ፌዴራሊዝም ስለመሆኑ ብዙ ምሁራንም ይስማማሉ፡፡ በእርግጥ ‹‹ፌዴራሊዝም በተለይ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ያለው የብሔረሰብ ፌዴራሊዝም ሠላምና አንድነት ያመጣል ወይስ ይበልጥ መቃቃርና መበታተንን ይፈጥራል?›› የሚለው ነጥብ ምሁራንን ሲያከራክር የቆየ ጥያቄ ነው፡፡ ክርክሩ አሁንም አልበረደም፡፡

ቀደም ሲል በዓለም አቀፍ ደረጃ በጣም የታወቁ ምሁራን ሳይቀር የብሔረሰብ ፌዴራሊዝም የዜጎችን መብት እንደሚያስከብር፣ ሠላምና አንድነትን እንደሚያረጋግጥ ጽፈዋል፤ ተከራክረዋል፡፡ ሐሳባቸውም የበላይነትን ለማግኘት በቅቶ ነበር፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ፋሽኑ አልፎ፣ የብሔረሰብ ፌዴራሊዝም ያስገኛቸዋል የሚባሉት በጎ ትሩፋቶች በሌሎች (ከብሔረሰብ ፌዴራሊዝም ውጭ በሆኑ) የፌዴራል ሥርዓቶችና በአሃዳዊ መንግሥታዊ አወቃቀር ጭምር ሊገኙ እንደሚችሉ የሚሞግቱ ምሁራን ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል፡፡ እንዲያውም የብሔረሰብ ፌዴራሊዝም ለሕዝቦች ግንኙነት እንቅፋትና ለአገር አንድነት አደጋ እንደሚሆንም በሰፊው እየተጻፈበት ነው፡፡

ናይጀሪያ በ1960 (እ.አ) ለመጀመሪያ ጊዜ የፌዴራል ሥርዓትን መከተል ስትጀምር የነበሯት ክልሎች ሶስት ብቻ ነበሩ፡፡ ነገር ግን በ1967 የቢያፍራ ግዛት ከናይጀሪያ መገንጠሏንና ይህንንም ማወጇን ተከትሎ፣ ከፍተኛ ደም አፋሳሽ ጦርነት ከተደረገ በኋላ የአገሪቱ ክልሎች ወደ 12 ከፍ እንዲሉ ተደርጓል፡፡ ከፍተኛ ቁጥር አለን በማለት በከፍተኛ የእርስ በእርስ ውድድርና ፉክክር ተጠምደው የአገሪቱን ሀብት የሚሻሙትን የሃውሳ ፉላኒ፣ የኢግቦና የዩሩባ ብሔረሰቦችን ትምክህት ለመቀነስ፣ በክልሎች መሀከል መመጣጠን እንዲኖር ለማስቻል፣ አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ሌሎች ብሔረሰቦች ዕድል ለመስጠትና የአገሪቱን ሠላምና አንድነት ለመጠበቅ ሲባል በ1996 ዓ.ም የክልሎች ቁጥር ወደ 36 እንዲያድግ ሆኗል፡፡ ሕንድም ብትሆን በተለያዩ ጊዜያት የክልሎችን ቅርጽ ለዋውጣለች፤ ሕጎቿንም እንዲሁ አሻሽላለች፡፡

ብዙ የፌዴራሊዝም ምሁራን እንደሚያስገነዝቡት የፌዴራል ሥርዓቱ የሰመረ እንዲሆን በክልሎች መካከል መመጣጠን ሊኖር ይገባል፡፡ እነናይጀሪያ ክልሎቻቸው የተመጣጠነ አቅም እንዲኖራቸው ያደረጉትም ይህንን ነጥብና ተሞክሯቸውን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ክልሎች በቆዳ ሥፋትና በሀብት በተቻለ መጠን የተመጣጠኑ ከሆኑ በመካከላቸው ትብብር እንጂ ልዩነት አይኖርም ወይም ይቀንሳል፡፡ ይህን መሠረታዊ መርሆ መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያን ሁኔታ ብንመረምረው የፌዴራል ሥርዓቱ ከፍተኛ ችግር ያለበት መሆኑን መገንዘብ እንችላለን፡፡

በኢትዮጵያ ክልሎች መካከል በጣም ከፍተኛ የመጠንና የሀብት ልዩነት አለ፡፡ ክልሎች ወይም ብሔረሰቦች የሚወከሉበት የብሔረሰቦች ምክር ቤትም ብሔረሰቦች ባላቸው ቁጥር ውክልና የተቋቋመ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት አንዳንድ ክልሎች እና/ወይም ብሔረሰቦች በፌዴራል መንግሥት ደረጃ ያላቸው ውክልናና ተጽዕኖ ከፍተኛ ሲሆን፣ የሌሎች አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ወገኖች ደግሞ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በአገር ደረጃ ድምጻቸው ምንም ዓይነት ተጽዕኖ የሌለው ክልሎች አሉ፡፡ ወሳኝና ወሳኝ ያልሆኑ አካላት አሉ ማለት ነው፡፡

ይህን ችግር ለማስተካከልና ክልሎች ተመጣጣኝ እንዲሆኑ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ የመገንጠልን አደጋ ወይም ማስፈራሪያ ለመቀነስ የግድ ሕገ-መንግሥቱን ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ ሕገ-መንግሥቱን ማሻሻል ግን እንዲህ ቀላል ነገር አይደለም፡፡ በሕገ-መንግሥቱ ላይ ለውጥ ለማድረግ የሕዝብ ተወካዮችና የፌደሬሽኑ ምክር ቤቶች በ2/3ኛ ድምጽ መስማማታቸው ብቻ አይበቃም፡፡ ለአንዳንዶቹ አንቀጾች የዘጠኙም ክልሎች ምክር ቤቶች ለሌሎች ደግሞ ከእነዚህ ምክር ቤቶች ሁለት 2/3ኛዎቹ መስማማት አለባቸው፡፡ ከዘጠኙ የሕገ-መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን አባላት አንዱ የነበሩት አምባሳደር ታዬ አጽቀ ሥላሴ እንደገለጹት (ሪፖርተር፣ ኅዳር 29/2006) በወቅቱ አቶ መለስ ዜናዊ ሕገ-መንግሥቱ በቀላሉ መሻሻል የለበትም የሚለውን ሐሳብ አጥብቀው ይደግፉት ነበር፡፡ እንደሚጠበቀውም የአቶ መለስ ሐሳብ ተቀባይነት በማግኘቱ ሕገ-መንግሥቱ በቀላሉ የማይሻሻል ሠነድ ለመሆን በቅቷል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራል ሥርዓት ችግር ግን በዚህ የተወሰነ አይደለም፡፡

## አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ዜጎች

‹‹የብሔረሰቦችን መብት ለማስጠበቅ የተደራጀ ነው›› የሚባለው የፌዴራል ሥርዓት የብዙ ብሔረሰቦችን መብት እየደፈጠጠ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በየክልሎች የሚኖሩት አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሌሎች ብሔረሰቦች መብታቸው እየተጠበቀ አይደለም፡፡ ከኢትዮጵያ ክልሎች በተነጻጻሪ የሁሉንም ሕዝብ መብት ለማክበር ጥረት የሚያደርጉት የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና የአማራ ክልሎች ናቸው፡፡ በሁለቱም ክልሎች አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብሔረሰቦች በልዩ ዞኖችና ወረዳዎች እየተደራጁ መብታቸው በተሻለ ሁኔታ ተከብሯል፡፡ በሌሎች ክልሎች በተለይ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል ግን የብዙኃን አምባገነንነት ሰፍኗል ማለት ይቻላል፡፡

በዚህ ክልል ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ወላይታ፣ ሀድያ፣ ትግራይ ወዘተ. ሕዝብ ይኖራል፡፡ 10 በመቶ የሚሆነው የክልሉ ሕዝብም አማራ እንደሆነም የማዕከላዊ ስታስቲክስ መረጃ ያመለክታል፡፡ ሆኖም የእነዚህ ነዋሪዎች መብት በምንም ዓይነት መንገድ አልተከበረም፡፡ ዜጎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩና እንዲዳኙ ሙሉ መብታቸው ተከብሯል በሚባልበት በአሁኑ ወቅት፣ ኦሮሚያ ውስጥ ይሄ የለም፡፡ የወረዳ ጥያቄ የሚያነሱ ወገኖች ጥያቄም በኃይል እንዲዳፈን ተደርጓል፡፡ እንዲያውም ዜጎች ማንነታቸውን የሚወስኑት ራሳቸው ናቸው በሚባልበት በዚህ ዘመን ኦሮሚያ ውስጥ ሌሎች ብሔረሰቦች ሥራ፣ መሬትና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት ማንነታቸውን ለመቀየር እየተገደዱ ነው፡፡

ይህ ሁኔታ በትግራይ፣ በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በአፋርና በሌሎች ክልሎች በሚኖሩ አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ዜጎች ላይ የሚፈጸም ግፍ ነው፡፡ ለምሳሌ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ሕዝብ ውስጥ 22 በመቶው አማራ ሲሆን፣ 13 በመቶው ደግሞ ኦሮሞ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የእነዚህ ወገኖች መብት በምንም ዓይነት ሲከበር አይታይም፡፡ ይልቁንም ዜጎች በአገራቸው እንደ መጤ እየተቆጠሩ ልዩ ልዩ በደልና ጥቃት ሲደርስባቸው ይታያል፡፡ ለተገፉትና በታሪክ ለተበደሉት ቆመናል የሚለው ሥርዓት አዳዲስ ተበዳዮችን እየፈጠረ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ነባርና መጤ የሚባሉት በአንትሮፖሎጂስቶች የተፈጠሩ አደገኛ ቃላትም ሕዝብ እንዲበደልና በዜጎች መካከል መቃቃር፣ ቁርሾና ጥላቻ እየፈጠረ ነው፡፡ እንዲያውም በአንዳንድ በደቡብ በጉራ ፈርዳ፣ በኦሮሚያ በአርሲና በወለጋ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝና በአፋር ክልሎች የተፈጸሙት (መጤ ናቸው በሚል ሰበብ) ዜጎችን ኢ-ሰብአዊ በሆነ መንገድ የማፈናቀል ሒደቶች ኢትዮጵያ ወደ ፊት ለመጠፋፋት (ኢትኒክ ክሊንሲንግ) አደጋ የተጋለጠች አገር እንድትሆን ሊያደርጓት ይችላሉ፡፡ የሌሎች አገሮች ተመክሮ እንዳስተማረን ጥላቻ ጥላቻን መውለዱ አይቀርም፡፡

በሐረሪ ክልል ያለው ሁኔታ ደግሞ እጅግ የተለየ ነው፡፡ በእርግጥ እዚያም ያለው አሠራር ‹‹ነባርና መጤ›› በሚለው ፍልስፍና የሚዘወር ነው፡፡ ሐረሪ ውስጥ በብዛታቸው ቀደምትነቱን የሚይዙት ኦሮሞና አማራ ብሔረሰቦች መሆናቸው ግልጽ ቢሆንም፣ የክልሉ ስም ሳይቀር አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ሐረሪዎች እንዲሰየም ተደርጓል፡፡ በሌሎች ክልሎች ያሉት አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብሔረሰቦች መብት ድምጥማጡ በሚጠፋበት እዚህ ክልል አነስተኛ ቁጥር ላላቸው የተለየ እድል የተመቻቸበት ሁኔታ ከተጠቀሰው የነባር-መጤ አስተሳሰብ የተወለደ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በዚህ ክልል ከተጠቀሱት ብሔረሰቦች በተጨማሪ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሌሎች ብሔረሰቦች አባላት በተለይ ጉራጌዎች እንደሚኖሩም ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ክልሉን የሚመሩትና አድራጊ ፈጣሪዎች ሐረሪዎች ናቸው እንጂ ሌሎች ብሔረሰቦች እዚህ ግባ የሚባል ድርሻ የላቸውም፡፡ አነስተኛው ብዙኃኑን የሚገዛበት ሥርዓት ከአፓርታይድ ሌላ ምን ሊባል ይችላል?

በኢትዮጵያ ሥልጣን የሀብት ምንጭ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ሥልጣን እና የብሔረሰብ ፖለቲካ ሲገናኙ ደግሞ ሁኔታው ሌላ ነው፡፡ አመራሮች ያላቸውን ሥልጣን የራሳቸውን ብሔረሰብ አባላት (ነባር የሚባሉትን) በልዩ ልዩ መንገድ እየጠቀሙ ሌሎች ወይም መጤ ተብለው የተፈረጁት ምንም እንዳያገኙ ያደርጋሉ፡፡ አገራችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከነናይጀሪያ እና ኬኒያ ጋር በሌብነት/ሙስና ተወዳዳሪ እንድትሆን ካስቻሏት ምክንያቶች አንዱ የብሔረሰብ ፖለቲካ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ እንዴት?

ሁላችንም እንደምናውቀው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ትልቅ ሀብት መሬት ነው፡፡ አሁንም ሁላችንም እንደምናውቀው፤ ብዙዎቹ ባለሥልጣናት በሙስና እየተጠረጠሩ የሚታሩትና የሚፈረድባቸው ከመሬት ጋር በተያያዘ ዝርፊያ ነው፡፡ አመራሮች መሬቱን ለግል መክበሪያነት ከማዋላቸው ባለፈ ብዙውን መሬት የእኛ ለሚሏቸው ሰዎች ነው የሚያቀራምቱት፡፡ ‹‹እስከ አሁን ተበድለናል፤ የምካስበት ጊዜ አሁን ነው›› የሚሉ አመራሮች እንዳሉ በብዛት የሚነገር አጀንዳ ነው፡፡

የኢሕአዴግ መሪዎች በኩራት እንደሚገልጹት፤ ፌዴራላዊ ሥርዓቱ አገሪቱን ከመበታታን ማዳን ብቻ ሳይሆን፣ ይህ ሥርዓት ከተተከለ በኋላ በብሔረሰቦች መሀከል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ተፈጥሯል፤ አገሪቱ በሠላምና በዕድገት ጎዳና መራመድ ችላለች ወዘተ.፡፡ በፌዴራላዊ ሥርዓቱ ላይ ጥናት ያደረጉ ብዙ ምሁራን እንደሚሉት ፌዴራላዊ ሥርዓቱ ለውጥ እያመጣ

> የብሔር ብሔረሰቦች በዓል በተከበረ ቁጥር የሚነገር ነገር አለ፤ ሁሉም የአገሪቱ ችግሮች በሕገ መንግሥቱ የተፈቱ ስለመሆኑ፤ የቀረው ሥራ ሕገ መንግሥቱ ሳይሸራረፍ እንዲተገበር መሥራት ብቻ ስለመሆኑ ጥናታዊ ጽሑፍ የሚያቀርቡ ሰዎችም ሆኑ ንግግር የሚያደርጉ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት በአጽንኦት ሲገልጹ ይስተዋላል

ስለመሆኑና አለመሆኑ፣ ሥርዓቱ ከኢሕአዴግ በኋላ ስለመቀጠል አለመቀጠሉ፣ ሠላም ስለማምጣት አለማምጣቱ ወዘተ. ማወቅ የሚቻለው ዴሞክራሲ ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ግን ኢሕአዴግ አፋዊ ከሆነ ዲስኩር ውጭ ቁርጠኛ አቋም እንደሌለው ብዙ አብነቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ቀደም ሲል አቶ ሌንጮ ለታ እንደገለጹትና በቅርቡ ደግሞ አምባሳደር ታየ አጽቀሥላሴ በሚገባ እንዳብራሩት፣ ኢሕአዴግ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓትን እንደሚከተል የሚገልጽ ቢሆንም፣ ከዚያም አልፎ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት በሕገ መንግሥት ደረጃ እውቅና እንዲያገኝ የሠራ ቢሆንም፣ ዋና ዓላማው ግን አሜሪካዊው የፖለቲካል ሳይንስ ምሁር ሳሙኤል ሃንቲንግተን ባስታወቁት መሠረት አንድ ፓርቲ ለረዥም ጊዜ የሚገዛበትን ሥርዓት መትከል ነበር፡፡

በወቅቱ ፕ/ር ሃንቲንግተን እንዳስገነዘቡት፣ ኢትዮጵያ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢዋ ከ2500 ዶላር በታች በመሆኑ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመገንባት አቅም እንደሌላት ጠቅሰው በኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት አውራ ፓርቲ የግድ ያስፈልጋል ብለው ነበር፡፡ የኢሕአዴግ መሪዎች የፕ/ር ሃንቲንግተን ምክር በሚገባ ተጠቅመውበታል፡፡ ወቅቱን ጠብቀው በየትኛውም መንገድ የሚያሸንፉባቸውን ምርጫዎች እያዘጋጁ ዴሞክራሲያዊ ለመምሰል ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ግን የፌዴራላዊ ሥርዓቱ ከኢሕአዴግ ህልውና ጋር የተሳሰረ ሳይሆን፣ ራሱን የቻለ ሥርዓት እንዲሆን የተደረገ ሙከራ የለም፡፡ ስለዚህም የፌዴራላዊ ሥርዓቱ ቀጣይነት ከኢሕአዴግ መኖር አለመኖር ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

አቶ መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት ስለፌዴራላዊ ሥርዓቱ ስኬቶች ተጠይቀው ሲመልሱ፣ ሥርዓቱ በመዘርጋቱ ዜጎች በማንነታቸው ኮርተው መኖር እንደቻሉ፣ የአንዱን ብሔረሰብ ሙዚቃ/ዜማ ሌላው እያጣጣመው ስለመሆኑ፣ በአገሪቱ ሠላም ስለመስፈኑ፣ እየተመዘገበ ያለው ዕድገት ከዚሁ ሥርዓት ጋር እንደሚያያዝ ወዘተ. ገልጸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አቶ መለስ የሚመሩት ኢሕአዴግ አባልና አጋር ድርጅቶች ምን ያህል ዜጋውን ጠርንፈው እንደያዙት አልገለጹም፡፡

የብሔር ብሔረሰቦች በዓል በተከበረ ቁጥር የሚነገር ነገር አለ፤ ሁሉም የአገሪቱ ችግሮች በሕገ መንግሥቱ የተፈቱ ስለመሆኑ፤ የቀረው ሥራ ሕገ መንግሥቱ ሳይሸራረፍ እንዲተገበር መሥራት ብቻ ስለመሆኑ ጥናታዊ ጽሑፍ የሚያቀርቡ ሰዎችም ሆኑ ንግግር የሚያደርጉ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት በአጽንኦት ሲገልጹ ይስተዋላል፡፡ ሁልጊዜም እንደምንሰማው፣ በአገዛዙ ባለሥልጣናት እምነት ሕገ መንግሥቱ ምንም እንከን የማይወጣለትና ሊሻሻልም የማይገባው ሕያው ሰነድ ነው፡፡ የፌዴራል ሥርዓቱ ከኢሕአዴግ በኋላ ሊቀጥል አይችልም ወይም ከፈጣሪው ጋር የሚሞት ሥርዓት ነው የሚባለውም በጉዳዩ ላይ ያልተቋረጠ ውይይት እየተደረገበት ባለመሆኑ ነው፡፡ እንዲያውም አገዛዙ ሕገ መንግሥት የማሻሻልን ጥያቄ የብሔረሰቦችን መብቶች እንደመደፍጠጥና የአገሪቱን አንድነት እንደመናድ አድርጎ ነው የሚቆጥረው፡፡

ለመሆኑ የገዥው ቡድን አመራሮች እንደሚሉት ፌዴራላዊ ሥርዓቱ በመተከሉ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መብቶች ተከብሯል? እንደሚነገረው ኢሕአዴግ ሥልጣን ላይ በወጣበት ዘመን ወደ 17 የታጠቁ (አብዛኞቹ የብሔረሰብ) ድርጅቶች ነበሩ፡፡ ነገር ግን የገዥው ኃይል መሪዎች እንደሚነግሩን የፌዴራል ሥርዓቱ ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ የአገሪቱ ሠላም ተረጋግጧል፡፡ የትጥቅ ትግል እናደርጋለን የሚሉ ደርጅቶች ቢኖሩም የፌዴራል ሥርዓቱ የሕዝቡን ጥያቄዎች በሚገባ ስለፈታቸው ውጤታማ መሆን እንዳልቻሉም በተደጋጋሚ ይገለጻል፡፡

ለመሆኑ ይህ ትንተና ውኃ ይቋጥራል? በአንድ በኩል የብሔረሰቦች ጥያቄ በማያዳግም ሁኔታ ከተፈታ ከ50 በላይ (ሕገ-መንግሥታዊና ከሕገ-መንግሥቱ ውጭ/በትጥቅ ለውጥ ለማምጣት) የተደራጁ የብሔረሰብ ድርጅቶች አሉ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የትጥቅ ትግሉ ለውጥ አላመጣም ማለት እውን ሕዝቡ አይወክላቸውም ማለት ነው ወይ? የኢሕአዴግ በተለይ የሕወሓት መሪዎች ልባቸው እያወቀ የማይናገሩት አንድ ዋና ነጥብ አለ፤ እነሱ ያካሄዱት የትጥቅ ትግል የፈለገውን ያህል ሕዝባዊ ድጋፍ ቢኖረውም፣ በአንድ በኩል የቀጠናውና የዓለም ዓቀፍ ሁኔታዎች ባይደግፏቸው በሌላ በኩል ደርግ በራሱ ችግር ተተብትቦ ባይወድቅ ለውጥ ሊያመጡ እንደማይችሉ ያውቁታል፡፡ ሌሎች ድርጅቶች እነዚህ ምቹ ሁኔታዎች አልገጠሟቸውም ማለት የሕዝብ ድጋፍ የላቸውም ሊባል ከቶ አይችልም፡፡

ሌላም ጥያቄ አለ፤ ‹‹የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ አንድነት ገንብተዋል፤ በብሔረሰቦች መሀከል መተማመን እንጂ ጥርጣሬ የለም›› የሚል ነጥብ በሰፊው ይነሳል፡፡ የገዥው ቡድን መሪዎች ይህን ይበሉ እንጂ እንደሚታየው ልዩነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ በመሄድ ላይ ነው፡፡ አሁን ኢትዮጵያውያን ከመቼውም ጊዜ በላይ በጥርጣሬ ዓይን የሚተያዩበት ዘመን ነው፡፡ ባንኩም፣ ሆስፒታሉም፣ የትምህርት ተቋሙም፣ ሆቴሉም፣ ስፖርት ክለቡም… በልዩነት እየተደራጀ ነው፡፡ ዋናው የሠራተኛ ቅጥር መሠረትም ብሔረሰባዊ ማንነት እየሆነ ነው፡፡ በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው አንድነታችን እየተጠናከረ ሳይሆን ለመለያየት እየተዘጋጀን ያለን ይመስላል፡፡ በብሔረሰብ በዓል ሰበብ ተወካዮች ናቸው የሚባሉት በስቴዲየም እየሰበሰቡ ድቤ መምታቱን ለጊዜው አቁሞ፣ ‹‹ከብተና አድኖናል የሚባለው ሥርዓት ለብተና እያዘጋጀን ነውን? በአገራችን ያለው ብሔራዊ መግባባት ወይስ ቂምና ቁርሾ?›› ወዘተ. ብሎ መጠየቅና በሰከነ ሁኔታ መወያየት የተገባ ይመስለናል፡፡

## እንግዳ

# “በብሔረሰቦች መካከል ያለው ግንኙነትና ጥላቻ በጣም የሚረብሽ ነው”

## ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም

**ገዥው ግንባር መቶ በመቶ አሸንፌበታለሁ ካለበት ከምርጫ 2007 በኋላ ያለውን አገራችንን የፖለቲካ ሁኔታ እንዴት ይገመግሙታል?**

ከምርጫ 97 በኋላ ነገሮች በጣም ተቀያይረዋል። ከዚያ ተስፋ ሰጪ ምርጫ ብዙዎቻችን ለአገራችን ከፍ ያለ ነገር ጠብቀን ነበር። ይሁን እንጂ ያው እንደታየው ሁሉም ነገር ምስቅልቅሉ ነው የወጣው። ያም ብቻ አይደለም፤ ገዥው ፓርቲ ከዚያ ምርጫ በኋላ ብዙ አሳሪ ሕጎችን በማውጣትና የዴሞክራሲ ሽግግሩን ሊያግዙ የሚችሉ ሂደቶችን ሁሉ በማፈን ተጠምዶ ነው የከረመው። ከምርጫ 2007 በኋላ ደግሞ እውነት ለመናገር ዴሞክራሲ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በራሱ በአገራችን ደብዛው ጠፋ። በዚህ ምርጫ ኢሕአዴግ ምርጫውን ሙሉ በሙሉ ምርጫውን አሸነፍኩ ካለ በኋላ የዴሞክራሲ ፍንጭ አለ ብሎ መናገርም አይቻልም። አንድ ፓርቲ ምርጫን መቶ በመቶ አሸነፍኩ በለበት ሁኔታ ውስጥ ዴሞክራሲ አለ ማለት በፍጹም የሚሆን ነገርም አይደለም፤ ተቃዋሚ ባለበት አገር አንድ ፓርቲ በምንም ዓይነት መልኩ መቶ በመቶ ሊያሸንፍም አይችልም። ኢሕአዴግ ምርጫውን በራሱ ኃይል ለራሱ የወሰደው ነው እንጂ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተፎካክረው ወድቀዋል ማለት አይቻልም። ሙሉ በሙሉ ኢሕአዴግ መውሰዱ በገሃድ የሚታወቅ ነገር ነው። የኔ ቃል ብቻ አይደለም፤ ዓለም በሙሉ የሚያውቀው ነው።

በቅርጽ ደረጃም ቢሆን የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ባለበት አገር ውስጥ አንድ ፓርቲ ሙሉ በሙሉ የሚያሸንፍበት ምርጫ የትም ቦታ ታይቶ አይታወቅም። በእርግጥ በሶብየት ኅብረት በራሽያ ኮሚንስት ፓርቲ በስታሊን ጊዜ እንዲህ ዓይነት ነገር ሆኖ ነበር። ስታሊን ግን አንድም ጊዜ ዴሞክራት ነኝ ብሎ ፎክሮ አያውቅም። ይህ ማንም ሰው ሊገነዘበው የሚችል ነገር ነው። ተቃዋሚዎች እያሉ አንድ ፓርቲ ምርጫውን መቶ በመቶ አሸንፌያለሁ ከማለት ምርጫውን ወስጀዋለሁ ማለት ይቀላል።

ሁኔታው ለአገራችን በጣም አደገኛ ነገር ነው። በፍጹም ከዴሞክራሲ ባህል ጋር የሚጣጣም አይደለም። ለአገራችን ሰላምም ጠቃሚ አይደለም። እንዲያውም በአገራችን ውስጥ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ሂደት ነው። በሰለማዊ ትግል በአገሪቱ ዴሞክራሲን እናሰፍናለን የሚሉ ተቃዋሚዎችን ተስፋ ያስቆርጣል። በሰላምና በዴሞክራሲ ተወዳድረው የሚያሸንፉበት መንገድ ከተዘጋ ሌላ የትግል መንገድ ይመርጣሉ። ያ የትግል መንገድ ደግሞ የኃይል ይሆናል። የኃይል ትግል ደግሞ ብዙ አደጋ እንዳለው ሁላችንም የምናውቀው ነገር ነው።



> አሁን እንደሚታየው እኮ ስንት የፓርቲ አባላትና አመራሮች ናቸው ማረሚያ ቤት ያሉት? የፓርቲ መሪዎቹን ወህኒ ቤት አጉሮ ሲያበቁ ‹‹ኑ እንነጋገር›› ማለት ምን ማለት ነው?

ወደ ዴሞክራሲያዊ መንገድ የሚመጣው የፖለቲካ ምህዳሩ ሲሰፋ ነው። የሐሳብ ነጻነት፣ ፓርቲ የማቋቋም፣ የመቀስቀስ፣ የማደራጀት መብት ሲከበር ነው። የፖለቲካ ምህዳሩ በዚህ መልኩ ከተዘጋ በምንም ዓይነት ወደ ዴሞክራሲ ልናመራ አንችልም። ይህ ደግሞ ለሰላማችን ጠንቅ ነው የሚሆነው። ኢሕአዴግ በአገራችን ሰላም እንዲሰፍን ፍላጎትና ቁርጠኝነት ካለው ፓርቲዎች በነጻ እንዲንቀሳቀሱ በወህኒ ቤት ማጎሩ ሁሉ መቆም አለበት። በየቦታው ዛሬ የምንሰማው እከሌ ታሰረ፣ የእከሌ ፓርቲ አባል ታሰረ፤ ተገደለ የሚል ነው። ይህ መቆም አለበት። እስከ መቼ ድረስ ነው በዚህ ልንቀጥል የምንችለው? ዛሬ እኮ 21ኛ መቶ ምእተ ዓመት ነው። በዚህ ዘመን አፍሪካን ጨምሮ በመላው ዓለም የሚገኙ ሕዝቦች ዴሞክራሲን በተወሰነም ደረጃ ቢሆን እያጣጣሙ ነው። እኛ ግን በመቶ በመቶ ምርጫ አሸንፌያለው በሚባልበት አገር ውስጥ ነው ያለነው። አገራችን በሚያሳዝንና በሚያሳፍር ሁኔታ በየጊዜው የፓርቲ አባላትና የፖለቲካ አክቲቪስቶች የሚታሰሩበት አገር ሆናለች።

**ገዥው ግንባር ‹‹ተቃዋሚዎች የፓርላማ ውክልና ባይኖራቸውም በወሳኝ አገራዊ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ ይደረጋል›› ማለቱ አይዘነጋም። ሰማያዊ ፓርቲና መድረክ በበኩላቸው በኢሕአዴግ በኩል የቀረበው ሐሳብ ማደናገሪያ መሆኑን ገልጸው እንደማይሳተፉ አሳውቀዋል። እርስዎ እንደገለልተኛ ዜጋ በገዥው ግንባር በኩል የተሰነዘረውን ሐሳብ እንዴት ይገመግሙታል?**

በመጀመሪያ ደረጃ የሚባለው ነገር ከንጹህ ልብ በመነጨ ስሜት ወይም ደግሞ ከሙሉ ፍላጎት ጋር የመጣ ነው ብዬ አላስብም። ምክንያቱም ውይይት ከመደረጉ ቀደም ብለው መሠራትና ተግባራዊ መሆን ያለባቸው ነገሮች አሉና ነው። ከሁሉ አስቀድሞ የጸረ ሽብር ዐዋጁ መሰረዝ አለበት። እሱ ሳይሰረዝ ማንም ምንም ዓይነት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ሊያደርግ አይችልም። አሁን በየቦታው እንደምናየው ወጣቶች ‹‹አሸባሪ›› እየተባሉ እየተከሰሱና እየታሰሩ ነው። ጸረ ሽብር ዐዋጁ እስኪሰረዝ ድረስ ማንም አፉን ሞልቶ ሊናገር አይችልም። ውይይት እኮ ነጻ መሆንን፣ በነጻነት ማሰብን፣ ሐሳብን በነጻነት ሳይፈሩና ሳይሸማቀቁ መግለጽን የሚጠይቅ ነገር ነው። ‹‹ይህን ብናገር ምን ይመጣብኝ ይሆን?›› እያልክ ራስክን ሳንሱር እያደረግህ ፍሬ ያለው ውይይት ልታደርግ አትችልም። ለዚህ ነው ከተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ውይይት ከመጀመሩ በፊት ቅድሚያ ተግባራዊ መሆን ያለባቸው ነገሮች አሉ የምለው። የፖለቲካ ምህዳሩን ማስፋት ያስፈልጋል። የንግግር ነጻነት መጠበቅ አለበት። ፓርቲዎች ያለፍርሃትና መሸማቀቅ በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ መፈቀድ አለበት። ይህ ከሆነ በኋላ ነው ኑና እንወያይ ማለት እንጂ እንዲያው በደፈናው የሚደረግ ነገር ውጤት አያመጣም።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች እኮ አንወያይም ሳይሆን ያሉት አንዳንድ ቅደመ ሁኔታዎችን ነው ያስቀመጡት። ፓርቲዎቹ በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ መፍቀድ ያስፈልጋል። አሁን እንደሚታየው እኮ ስንት የፓርቲ አባላትና አመራሮች ናቸው ማረሚያ ቤት ያሉት? የፓርቲ መሪዎቹን ወህኒ ቤት አጉሮ ሲያበቁ ‹‹ኑ እንነጋገር›› ማለት ምን ማለት ነው? ከማን ጋር ነው ውይይት የሚደረገው? መጀመሪያ እነሱን መልቀቅና የፖለቲካ ምህዳሩን ሰፋ ማድረግ ያስፈልጋል። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት እንደ ጸረ ሽብር ዐዋጅ ያሉ የዜጎችን መብት የሚገድቡ ዐዋጆችንም መሰረዝ ያስፈልጋል። ከዚያ በኋላ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከመንግሥት ጋር ሊወያዩም ሐሳብ ሊለዋወጡም ይችላሉ። ለአገራችን የሚጠቅምና የዴሞክራሲ ሂደቱን ሊያግዝ የሚችል ፍሬ ያለው ውይይት መጠበቅ የሚቻለውም ከዚያ በኋላ ነው።

**በአገራችን ምርጫ ሲመጣ ብዙ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና አባላትን እንዲሁም ጋዜጠኞችና አክቲቪስቶችን ማሰር፣ ከምርጫ በኋላ ክሱን ማቋረጥና በምህረት ወዘተ. መልቀቅ እየተለመደ መጥቷል። አካሄዱ ከሕግ አንጻር እንዴት ነው የሚታየው? በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት/ትግል ላይስ ምን አይነት አንድምታ አለው ይላሉ?**

ለዴሞክራሲ ግንባታ፣ ለሰላምና ለልማት እንዲህ ዓይነት እንቅስቃሴ መልካም አይደለም። ሰውን አስሮ በይቅርታ መፍታት ምን ማለት ነው? መጀመሪያ ነገር መታሰር አልነበረባቸውም። ፖለቲከኞች፣ አክቲቪስቶችና ጋዜጠኞች የሚታሰሩባቸው ጉዳዮች የሚያሳስሩ ናቸው ወይ? አንድ ሰው መብቱን ስለጠየቀ፣ የአንድ ፓርቲ አባል ሕጉ በሚፈቅደው መልኩ ስለተንቀሳቀሰ መታሰርም መቀጣትም የለበትም። በሆነ ባልሆነው አስሮ በይቅርታ ለቅቄያለሁ ማለት ቀልድ ብቻ ሳይሆን በዜጎች ሕይወት ላይ መጫዎትም ነው። የሕዝብ ውክልና ባለው መንግሥት እንዲህ ዓይነት ነገር አያደርግም። ጥፋት ከተሠራ ማንም ሰው በዚያ ወንጀል ይቀጣል። ያጠፋ ወይም ወንጀል የሠራ ሰው አይጠየቅ፤ አይቀጣ የሚል አካል የለም። ጥያቄው ሂደቱ አገዛዙ ስለፈለገው የሚፈጸም ስላልፈለገው የሚቀር መሆን የለበትም የሚለው ነው።

ወደ ይቅርታ ስንመጣ፣ እርግጥ መንግሥት በይቅርታ ሊለቅ ይችላል። ይኼ በሕገ መንግሥቱም ያለ ነገር ነው። ነገር ግን በአገራችን ጉዳዩ ቀልድ እየሆነ መጥቷል። ሰዎች ይታሰራሉ በይቅርታ ይፈታሉ ይባላል። ደግሞም በይቅርታ የማይፈቱ አሉ። አሁን ለምሳሌ ውብሸት ታየ በይቅርታ ይለቀቃል ተብሎ ይቅርታ ጠይቆ ነበር፤ ግን እስከዛሬ አልተለቀቀም። ይቅርታ ከጠየቅክ ትፈታለህ ብለው ቃል ገብተውለት ነበር፤ ግን አልተፈታም። ባለቤቱ ይህን በሚመለከት ሰሞኑን ተናግራለች። እና በእውነቱ እየሆነ ያለው ሁሉ ከአንድ መንግሥት የሚጠበቅ አይደለም። የለየለት ውንብድና ነው እያየን ያለነው።

**እነሀብታሙ አያሌው ፍርድ ቤት በነጻ ቢያሰናብታቸውም እስካሁንም አልተፈቱም። ይህስ ከሕግ አንጻር እንዴት ነው የሚታየው? ተጠርጥረው በቁጥጥር የዋሉ ዜጎችን በሚመለከት ፍርድ ቤት ብያኔ ሳይሰጥ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት (ቀደም ሲል አቶ መለስ፣ አሁን ደግሞ አቶ ኃይለማርያም …) ‹‹ወንጀለኞች ናቸው፤ አሸባሪዎች ናቸው›› የሚሉት ነገር አለና፣ አካሄዱ ስለአገራችን የፍትሕ ሥርዓት የሚነግረን ምንድን ነው?**

በመሠረቱ አንድ ሰው በፍርድ ቤት ሳይፈረድበት ክስ ቀርቦበት እየተከላከለ እያለ ወንጀለኛ ነው ማለት ተገቢ አይደለም፤ ሕገ ወጥነትም ነው። እነዚህ ሰዎች፣ አቶ ኃይለማርያምም ሆኑ አቶ መለስ በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ ሰዎችን እየጠቀሱ ‹‹ወንጀለኞች ናቸው›› ብለው ሲናገሩ የፍርድ ሂደቱን አደናቅፈዋል። አካሄዱ በዳኞች ሥራ ላይ ጫና መፍጠር እንደሚፈጥር የሚያጠራጥር አይደልም። መታወቅ ያለበት ደግሞ ዳኞችን የሚሾሟቸው እነኝህ ሰዎች ራሳቸው ናቸው። እንደ እንግሊዝና አሜሪካ ባሉ ያዳበረ ዴሞክራሲ ባለባቸው አገሮች ውስጥ ያለውን እንተወውና ጀማሪ ዴሞክራሲ በሚባሉት እንደ ጋና ባሉ አገሮች ውስጥ እንኳ የአገር መሪ በፍርድ ሂደት ላይ ‹‹ወንጀለኛ ናቸው›› ብሎ ቢናገር ክሱ ወዲያውኑ ይሰረዝ ነበር። ምክንያቱም አንድ መሪ የተናገረው በዳኞቹ ላይ ጫና ይኖረዋልና ነው። አቶ መለስም ሆኑ አቶ ኃይለማርያም ይህን ከተናገሩ በኋላ ዳኞቹ ፋይሉን መዝጋት ይገባቸው ነበር።

ወደ ገፅ 7 ዞሯል

## ነጻ አስተያየት

በወንድማገኝ አንጁሎ
የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ መምህር

# መርዝን በማር ለውሶ ለማስዋጥ ከመሞከር በስተጀርባ

ሃፍቶም ገ/ኪሮስ የተሰኘ ግለሰብ በቅርቡ ‹‹የኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወቅታዊ ተግዳሮቶች'›› በሚል ርእስ አንድ ጽሑፍ በፌስቡክና በአይጋ ፎረም የመረጃ ድረ ገጾች እንዲሁም ተልዕኮ የመስጠት ያህል በአንዳንድ የዩኒቨርስቲያችን መምህራን ኢ-ሜይል አድራሻቸው በመጻፍና በመላክ ማስነበቡ ይታወቃል:: በጽሑፉ ከመጀመሪያው እስከ 5ኛው ገጽ አንቀጽ 2 ድረስ በተጠቀሱ ሐሳቦች ውስጥ አገራችን ትላንትና የነበራት እንዲሁም ዛሬ ያላት ገጽታዎቿ በበቂ ሁኔታ ተነጻጽረው የተገለጹ ከመሆናቸውም በተጨማሪ መንግስት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መስፋፋት የሰጠው ትኩረትና ከተቋማቱ የሚጠበቁ ሥራዎች በአግባቡ በመገለጻቸው መልካም ነው እያልኩኝ ነገር ግን ከላይ ከተጠቀሰው ገጽና አንቀጽ ጀምሮ የተፃፉት ማለትም «አካባቢነትን መሠረት ባደረጉ ሹመቶች ዙሪያ» ሐሳቦች ከመንግሥት ዕይታና ከአፈጻጸም ትግበራ አንጻር በተጨማሪም ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲያችን ተጨባጭ እውነታ ጋር በማነጻጸር በዝርዝር መመልከቱ መልካም ይመስለኛል::

በአሁኑ ሰዓት በአገራችን ባሉት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ እንደ አደጋ ከሚታዩ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ውስጥ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችና የኪራይ ሰብሳቢነትና የሙሰኝነት አደጋዎች ዋነኞቹ እንደሆኑ አያሌ ማስረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል:: ይህንን ስል ግን ከማናቸውም የሹመት አሰጣጥ ሒደቶች ጋር በተያያዘ እንደተባለውም አካባቢን መሠረት ባደረገ መልኩ የሚከናወኑ ሹመቶች ከአፈጻጸማቸው ረገድ በሁሉም ባይሆን በተወሰኑ ዩኒቨርስቲዎች የተወሰኑ ክፍተቶች እንደሚኖሩት ይገመታል:: ከላይ ለተነሱትም ዋና ችግሮች መነሻም እንደሚሆን ግልጽ ነው:: ለአብነትም ምንም እንኳን መንግሥት የማረምና የማበቃት ሥራዎችን እየሰራባቸው ቢያቀናቸውም ሕዝቦች ብዝሃነትን ጠበቀው በሚኖሩባቸው አያሌ ከተሞችም በአካባቢ ሰዎች በመመራታቸው የተነሳ ልክ እንደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አልፎ አልፎም ቢሆን የአፈጻጸም ጉድለቶች እንደሚታይባቸው ይታወቃል:: እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ግን እንዲያው በደፈናና በጅምላ በአመዛኙ ሚዛን የማይደፋ ሐሳብን አንስቶና በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚታይ አሳሳቢ ችግር ነው ብሎ ሀተታ ለማብዛት መሞከሩ እንደ አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲያችን ተጨባጭ ሁኔታ ስመለከት ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ዓይነት ከመሆኑም በላይ በመረጃና በጥናት ያልተደገፈ አሉባልታም ነው ለማለት እደፍራለሁ::

በግለሰቡ የተጻፈው ጽሑፍ አድራሻው አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ እንዲሁም ግለሰቡ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ የሚሠራ መሆኑን ለሚገነዘብ አካል ቢያንስ በጽሑፉ የተነሳው ችግር እንደ መነሻነት በዩኒቨርስቲያችን ውስጥ እየታየ ያለ የዩኒቨርስቲያችንም ዐቢይ ተግዳሮት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላልና ምንም እንኳን ጽሑፉ የአለ በጅምላን ካባን የደረበ ቢሆንም ችግሩን ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲያችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ትርጉም ሰጥቶ ማየቱና መዳሰሱ ተገቢ አካሄድ ይመስለኛል:: ጸሐፊው በጽሑፉ በአገራችን እየተካሄደ ያለውን የፌደራሊዝም ሥርዓት ግንባታን ከመጻረሩ ጋር በተያያዘ ከጀርባው የተሸከማቸውን ድብቅ ዓላማዎቹን ለማሳካት ያስችለው ዘንድ ጥረት እያደረገ ስለመሆኑ የሚከተሉትን አብነቶች መመልከት ይቻላል:: እነዚህም ጸሐፊው በጸሑፉ በተዘዋዋሪ መንገድም ቢሆን መንግሥትን ለማዘዝ መሞከሩን፣ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲያችን ላይ ከውሳኔ ረገድ የሌለውን ያለ በማስመሰል መንግሥትን ለማምታት ግራ ማጋባቱን፣ የዩኒቨርስቲያችን ማኅበረሰብ የተሳሳተ መረጃ እንዲደርሰው በማድረግ ለመደለልና ለማነሳሳት ብሎም በውጭ ያለው ኅብረተሰብ ስለዩኒቨርስቲያችን የተሳሳተ ገጽታ አንዲኖረው ለማስቻል ጥረት ማድረጉን መጥቀስ ይቻላል::

መቼም ለውጥ ሲጠበቅ በቅድሚያ ራስን መመልከቱ መልካም ይመስለኛል:: በድርጅትና በተማሪዎች ኅብረት እንቅስቃሴ ስም ባለተገባ የመጀመሪያ ድግሪ ውጤት መምህር፣ የኮሌጅ የምርምር ጽ/ቤት ኃላፊና የዩነቨርስቲው ፈላጭ ብሎም ቆራጭ እየተኮነ በተጨማሪም ከሌሎች የኮሌጆች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በተለየ መልኩ መኪና አስመድቦ እንደተፈለገ እየተገባና እየተወጣ ይህ አነሰ ተብሎ በዩኒቨርስቲያችን ውስጥ ግለሰቡ ባለው ያልተገደበ መብት የሌለን እንዳለ አድርጎ ለማሳየት መሞከሩ ከጀርባው በተጨማሪነት ያዘለው ድብቅ ዓላማ ግለሰቡ እንዳለው ይህ ማሳያ ሊሆን ይችላል ብዬ አምናለሁ::

> በእርግጥ በአሁኑ ሰዓት በርካቶች በሕይወት ዘመናቸው እንዲኖሯቸው ከሚፈልጉዋቸው ነገሮች መካከል ሥልጣን አንደኛው እንደሆነ የሚታወቅ ቢሆንም በአመዛኙ ሊባል በሚችል መልኩ አብዛኞቹ ሥልጣን ፈላጊዎች አገራቸውንና ሕዝባቸውን በአግባቡ በመምራት ለመጥቀም በማሰብ ሳይሆን በሥልጣን ውስጥ ያሉትን ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ካላቸው ከፍተኛ ፍላጎት በመነሳት እንደሆነ ይታወቃል

በአንድ ወቅት ማለትም በ2003 ዓ.ም. የዩኒቨርሰቲ ኃላፊዎችን ከቦታቸው መነቃነቅን ተከትሎ አንድ አጀንዳ በዩኒቨርስቲያችን ውስጥ ሲራመድ እንደነበር ይታወቃል:: ይህም አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሚሠራው አብዛኛው ስታፍ ከሰሜን የመጣ ስለሆነ ይህ ተቋም ተረጋግቶ እንዲመራ ከተፈለገ አብዛኛውን ማለትም ከሰሜን የመጣውን ማኅበረሰብ በሚወክል መልኩ ተቋሙ መምራት አለበት የሚል ነበር:: ምንም እንኳን «አብዛኛውን በሚወክለው» በሚለው በግለሰብ ወይም በቡድን ሐሳቦች የሚራመድ የመንግሥት አቅጣጫ ባይኖርም በአካባቢ ሰዎች መንግሥታዊ ተቋማት (ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ጨምሮ) አንዲመሩ በመንግሥት ዘንድ መደረጉ ራሱን የቻለ ግልጽ የሆነ ምክንያት መኖሩን በመገንዘብ በወቅቱ እኔ በግሌ ሐሳቡን ካነሱ ግለሰቦችና ከጸሐፊውን ጋር ተቋማት በእውቀትና በችሎታ ሊመሩ እንደሚገባ ተስማምቼ ነገርግን ዕውቀቱም ችሎታውም ኖሯቸው የአካባቢ ሰዎችም ሆነው በሚሩና ለእነሱ ቅድሚያ ቢሰጣቸው እንደማልቃወም በመግለጽ ይህ ካልሆነ ግን እንዲያው በጭፍን አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ላይ ብቻ ተዓምር ይፈጠር መባልን እንደማልደግፍ ነገር ግን ተዓምር ይፈጠር ከተባለ ግን በተመሳሳይም መቀሌ ዩኒቨርስቲ በኦሮሞ ምሁር፣ ባህር ዳርም በደቡብ ምሑር እንዲመራ አስችሉና እዚህ አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ከእነሱ ልምድ በመውሰድ በተግባራዊነቱ ዙሪያ በጋራ እንደምንታገል ሐሳብ በመስጠት መከራከሬ ትዝ ይለኛል::

በመቀጠልም ይህ ኃላፊዎች ከወንበራቸው የሚነቃነቁበትን ወቅት በመጠበቅ የሚነሳው «በአካባቢ መመራት» የሚል የስሞታ አባዜ በተመሳሳይም በ2004 ዓ.ም. ዶ/ር ዮሴፍ ብሩ ዩኒቨርስቲውን እየመራ በነበረበት ወቅትም የተከሰተ ከመሆኑም በላይ በወቅቱም በተመሳሳይ መልኩ በተደራጁ ቡድኖች አማካይነት በዩኒቨርስቲው ቦርድ ሰብሳቢ በአቶ ታገሰ ጫፎና በአቶ ስምዖን ሽብሩ ላይ ያነጣጠረ ግን ጋሞ-ኦቾሎን ያወገዘ (ጋሞ መምራት አይችልም ዓይነት አንድምታን የያዘ) ፅሑፍ ብዛት ላላቸው ነገር ግን ለተመረጡ የዩኒቨርሰቲ መምህራን በኢ-ሜል አድራሻቸው እንዲሁም በሪፖርተር ጋዜጣ መለቀቁ ይታወቃል:: ቀጥሎም በ2006 ዓ.ም. በዩኒቨርስቲው በተነሳው ረብሻ አማካኝነት አሁን ድረስ የዩኒቨርስቲው በመምራት ላይ የሚገኙትን ዶ/ር ፈለቀ ወ/የስ ከቦታቸው መነሳታቸው አይቀርምና በሚል አሳቤ በቀጣይ ሊሾም ስለሚገባው ግለሰብ ማንነት ሒሳብ መሥራት የጀመረው ይህ ቡድን በተመሳሳይ መልኩ ከመንቀሳቀሱም ባሻገር አጀንዳውን እስከማይመለከታቸው ተማሪዎች በማድረስ በወቅቱ ስታዲየም በመገኘት ረብሻውን ለማርገብ ለሞከሩት የዩኒቨርስቲ ቦርድ ሰብሳቢ ለተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ ጉዳዩ እንዲነሳ መደረጉ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው:: በነገራችን ላይ ይህ ቡደን ሁለት ፊት ያለው ሲሆን አጀንዳውን ሲያራምድ ከዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንቱ ጉያ ሥር ተሸጎጦም ጭምር እንደነበር ሁላችንም ያስተዛዘበ ክስተት ነበር::

በወቅቱም ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት በሚል ወደ ዩኒቨርስቲያችን የመጡት የኢፌድሪ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር የተከበሩ አቶ ሺፈራው ሽጉጤ በዩኒቨርስቲያችን በተገኙበት የተቋሙ የግምገማ መድረክ ላይ ይህ የፕሬዚዳነትነት ሥልጣን ለምን ለአካባቢ ምሁራን የሚል ጥያቄ በመነሳቱ የተከበሩ ሚንስትር ጥያቄው በተመሳሳይ መልኩ በ2005 ዓ.ም. ክረምት ላይ በአዲስ አበባ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሰቲ በተሰጠው የአመራሮች ሥልጠና ላይ በአንድ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ መምህር መነሳቱን አስታውሰው አሁንም በድጋሚ መነሳቱ ገርሟቸው የሚከተለውን ወርቃማ አባባል በመናገር ነበር የቡድኑን ሴራ ያከሸፉት:: «ዕውቀቱ ኖሮት ነገር ግን በአካል ሳይሆን በአስተሳብ የተጣመመ ጋሞ ካለ አቅንተነውና አብቅተነው ዩኒቨርስቲውን እንዲመራ እናድረጋለን ነበር» ያሉት:: ይህን አባባል ወርቃማ ነው ያልኩት ተቋሙ በጋሞ ይመራል ስለተባለ ደስታ ተሰምቶኝ ሳይሆን የአመራር ምልመላው ዕውቀትን፣ የትምህርት ደረጃን እንዲሁም ግለሰቡ ለአካባቢው ያለውን ቅርበት ከግንዛቤ ባስገባ መልኩ መግባባት ተፈጥሮ በሁሉም ዩኒቨርስቲ እየተተገበረ ያለ በመሆኑና በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብቻ የተለየ ነገር ይፈጠር ብለው ለሚያቀነቅኑ ኃይሎች ቆንጆ ምለሽ እንደሆነ በማመኔ ነው::

በተመሳሳይም በያዝነው 2008 ዓ.ም. በምክትል ፕሬዚዳነት ደረጃ ያለውን የኃላፊነት ክፍተት ቦታ ለመቆናጠጥ በተሰላው ስሌት መሠረት ገና ለገና እነ እከሌ የተባሉ የጋሞ አካባቢ ምሁራኖች ከሌላ ዩኒቨርስቲ ተዛውረው መጥተዋልና በሚል እሳቤ የመምህራኑን ብሎም በተዘዋዋሪ መንገድ የዩኒቨርስቲውን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ ጽሑፍ በግለሰብ ነገር ግን ከጀርባው ሌላ ተልዕኮና ኃይል እንዳለ በሚያሳብቅ መልኩ መለቀቁ ለድብቅ ዓላማ ስኬት ተብሎ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል:: በመሠረቱ ከዩኒቨርስቲዎች ወደ አካባቢያቸው የተዘዋወሩ መምህራን የጋሞ ብሔር ተወላጅ ምሁራኖች ብቻ አልነበሩም:: ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲም ብዛት ያላቸው መምህራኖች በሹመትና በተለያዩ የግልና የቤተሰብ ምክንያቶች ወደ አካባቢያቸው መዘዋወራቸው ይታወቃል::

ለአብነትም ዶ/ር ይሻሙና ዶ/ር ዓለማየሁ ጩፋሞ (ተመልሶ ቢመጣም) ወደ ዋቻሞ ዩኒቨርስቲ በሹመት፣ ዶ/ር ዳዊት ወደ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ በሹመት መሄዳቸው እየታወቀ በቅርቡ አንድ የጋሞ ተወላጅ ወደ አካባቢው በመምጣቱ ወደ አካባቢ መዘዋወር ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተ እስኪያስመስል ድረስ አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ተቀምጦ ባልተረጋገጠ የመረጃ መነሻነት የጠቅላላ ዩኒቨርስቲዎችን ገጽታ በሽፋንነት በመጠቀም ጽሑፍ መጻፍን ምን ይሉታል? ለምንስ እነዚያና ሌሎች መምህራን ወደ አካባቢያቸው ሲዘዋወሩ ያውም የመመህራኑ መሄድ ከማንም በላይ ዩኒቨርስቲያችንን የጎዳ ተግባር እንደሆነ እየታወቀ መሰል ጽሑፎች ለሁሉም ትምህርት ተቋማት በመቆርቆር እሳቤ በእነዚያ ጊዜያቶች ስለምን አልተጻፉም ነበር?

የሚገርመው የሥልጣን ወንበር መነቃነቅን ብቻ ተክትሎ አልነበረም ጽሑፎችና የቅስቀሳ ወሬዎች በዘመቻ መልክ በዩኒቨርስቲያችን የሚለቀቁት:: አጋጣሚ ሆኖ በምክትል ፕሬዚዳንትነት፣ በአማካሪነት አልያም በዳይሬክተርነት አንድ የአካባቢው ሰው ከተሾመ የወሬ ዘመቻው በማሸማቀቅ ታግዞ በግቢ ውስጥ እንደፈለ ነበር የሚነዛው:: ለአብነትም ዶ/ር ዳምጠው ደርዛ የአካዳሚክ ም/ፕሬዚዳንት አማካሪ፣ አቶ ዮሐንስ ትግሮ የት/ጥ/ማ/ዳ/ጽ/ቤት ዳይሬክተርና አቶ ብሩክ ግስላ የይዞታ ልምት ዳ/ጽ/ቤት ዳይሬክተር በሆኑበት ሰዓት በግቢ ውስጥ የተነዛው ወሬ እጅጉን አስገራሚ ሆኖ ያለፈ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ሲሆን በተመሳሳይ ግን ዶ/ር ጳውሎስ ታደሰ የተማሪዎች አገ/ዳ/ጽ/ቤት ዳይሬክተር ያውም ያለውድድር፣ ዶ/ር የቻለ ከበደ የአስ/ጉ/ምክትል ፕሬዚዳንት ሲሆኑና ሌሎች ሹመቶች ጸሐፊ ነኝ ተብየውንም ጨምሮ (የተ/ሳ/ኮሌጅ የምርምር ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊና ግለሰቡ ባለው የስልጣን ጥማት ስንት አንጋፋና የዩነቨርስቲውን መላ ማህበረሰብ ሊወክሉ የሚችሉ ስመ ጥር መምህራን ባሉበት ተቋም የመምህራን ማኅበር ፕሬዚዳንትነትን የሙጢኝ ብለው ይዘው ሲቀመጡ) አንዳች የወሬ ደምፆችና ጽሑፎች አለመደመጣቸው ማናችንንም ያስተዛዘበ ጉዳይ ነው::

እዚህ ላይ እኔም እንደጸሐፊው በመረጃ ረገድ የማላውቃቸውን የአገራችንን ዩኒቨርስቲዎች ተጨባጭ ሁኔታ ለመዘርዘር ባልደፍርም በዩኒቨርስቲያችን ተጨባጭ ሁኔታ በመመርኮዝ ግን መንግሥት ከጸሐፊው መልዕክት በስተጀርባ የተደበቀውን ሴራ ይመረምር ዘንድ አቤት እላለሁ:: ድንገት መንግስት ያሰበውን ሳይሆን ግለሰብ ወይም ቡድን ያሰበውን ሰው በማሾም ትስስርን ለማጥበቅና ዕድሜን ለማራዘም ታስቦ ቢሆንስ? በመሆኑም በዩኒቨርስቲያችን ያለውን ብዝሃነት ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የተፈጠረውን የአብዛኛውን ማህበረሰብ ተከባብሮና ተቻችሎ የመኖር ታሪክ ለመናድ በተደጋጋሚ ግዜያቶች ጸሐፊውን ጨምሮ ሌሎች ግለሰቦችም የሚደረጉት ሕገ መንግሥታዊ ጥሰቶችና አላግባብ አካሄዶች ከወዲሁ ‹‹ሃይ!›› ሊባሉ የሚገባቸው በመሆኑ የዩኒቨርስቲው ቦርድና የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ለጉዳዩ ትኩረታቸውን እንዲሰጡ ጥሪዬን እያስተላለፍኩኝ አውቆም ይሁን ሳይውቅ ባልተደገፈ መረጃ እነዚህንና መሰል አስተሳሰቦችን እንዲያራምዱ በብብቱ አቅፎ ድንጋይ የሚያስወረውረውን የዩኒቨርስቲያችንንም አመራር በተጨማሪም ለአካባቢው ማናቸውም ጥቅሞች ሊቆም ሲገባው ነገር ግን አጋጣሚዎችን በመፍጠርና በማስፈጠር ድብቅ ዓላማን ለማስኬድ የሚደረጉ የአመራር ቁመናዎች ዩኒቨርስቲው ለተመሰረተበት የአካባቢው ሕብረተሰብ እንደ ንቀት የሚታይ በመሆኑ መንግስት የዩኒቨርስቲውን ቁመና ከተዘረጋው ኔትወርክ ጋር ሊፈተሽ ይገባል እላለሁ::

በኢፌድሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 39 (3) መሠረት ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአካባቢያቸው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት መንግስታዊ ተቋማትን

ወደ ገፅ 8 ዞሯል

## ነጻ አስተያየት



መስከረም አበራ

# "ዘመን የመጣላት" በርማ

በዓለም ዳርቻ ስለ አምባገነናዊ የመንግሥት አስተዳደር ዘይቤ ሲነሳ የቀድሞዋ በርማ የአሁኗ ሚያንማር ፊታውራሪነቱን ትወስዳለች፡፡ ከአምባገነንነትም የወታደራዊ አምባገነንነትን ዳፋ የተሸከመችው እስያዊቷ አገር እስከ እ.ኤ.አ. 1948 የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነበረች፡፡ ከታላቋ ብሪታኒያ የተገዥነት ቀንበር ስትላቀቅ ታዲያ ያረፈባት የነጻነት ጮራ ሳይሆን የአገር በቀል ወታደራዊ አምባገነኖች መዳፍ ነው፡፡ በርግጥ ከቅኝ ግዛት ማግስት ለዐሥራ አራት ዓመታት (ከ 1948-1962) አገሪቱን የመራው በአሁኑ ወታደራዊ መንግሥት ክንድ የተወገደ የሲቪሊያን መንግሥት ነበር፡፡ ይህ መንግሥት አገሪቱን ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ያወጡ የነጻነት አባቶች የመሠረቱት መንግሥት ነበር፡፡ የአሁኗ የበርማ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ሳን ሱቺ አባት አን ሳንግ የሲቪሊያኑ መንግሥት ዋና የነበሩ የጸረ-ቅኝ ግዛት ታጋይ ነበሩ፡፡ ሰውየው በአገሪቱ የሚገኙ ብሔረሰቦች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ ይለፉ የነበሩ ፖለቲካኛ እንደነበሩ ይነገርላቸዋል፡፡

የሲቪሊያኑን መንግሥት በመፈንቅለ መንግሥት አሸቀንጥሮ ጥሎ በ1962 ሥልጣን የያዘው ወታደራዊ መንግሥት ስልሳ ለሚጠጋ ዓመት በርማን ቀጥቅጦ ገዝቷል፡፡ እንደማርያም መቀነት የረዘመ ዕድሜ ያስቆጠረው ከፊል ወታደራዊ መንግሥት አፋኝ አስተዳደር አገሪቱን በእጅጉ ጎድቷታል፡፡ በኢኮኖሚው እንደነብር የሚሸመጥጥ የኢኮኖሚ እድገት አላቸው በሚባሉት የምሥራቅ እስያ አገራት ክልል ውስጥ የምትገኝ እንደ ኤሊ የሚሳብ ኢኮኖሚ ያላት ደሃ አገር አድርጓታል፡፡ በፖለቲካው ረገድም የዘር ግጭት፣ የፕሬስ አፈና፣ የሰብአዊ መብት ረገጣ፣ መንግሥታዊ ሙስና፣ ስደት የተንሰራፋባት የመከራ ምድር መሆኗ በእስያ የከተመችውን አገር አፍሪካዊ ምድር የሚያስመስሏት ገጽታዎቿ ናቸው፡፡ የበርማ ፖለቲካ ከአገራችን ታሪካዊም ሆነ ወቅታዊ ፖለቲካ ጋር የሚያመሳስላት ምልክት እጅግ ነው፡፡ የብሔር ፖለቲካ ጦስ፣ መንግሥታዊ ባለጠግነት፣ የዴሞክራሲ የዘወትር ልጅነት፣ ፈርጣማ ወታደራዊ ጡንቻ ያጀበው መንግሥታዊ አስተዳደር፣ ተቃዋሚን ማሳደድ፣ ሕዝባዊ ስደት፣ የፕሬስ አፈና፣ የሰብአዊ መብት ጥሰት ወዘተ. ሁለቱን አገራት መንታ የሚያስመስሉ ፖለቲካዊ እውነታዎች ናቸው፡፡

## የብሔር ፖለቲካ ጦስ

በርማ በሦስት ዲጅት የሚቆጠር (100) ብዛት ያላቸውን ብሔሮች በማቀፍ የብሔሮች መናኸሪያ ነች ከምትባለው አገራችን ትልቃለች፡፡ በርካታ ብሔሮችን ያቀፉ መሆናቸው ሁለቱን አገሮች የሚያመሳስላቸው ሲሆን በሁለቱም ዘንድ የአንድ ዘር የበላይነት አለ ብሎ የሚያምን የዘር ፖለቲካ ፈለግ መኖሩ የአገራቱን ፖለቲካዊ ቅኝት እጅግ ያቀራርበዋል፡፡ አገሪቱ የቀድሞ ስሟን ያገኘችበት ‹‹በርማ›› የሚባለው ብሔር 60 በመቶ የሚሆነውን የአገሪቱን ሕዝብ ብዛት ይይዛል፡፡ ይህ ብሔር ለረዥም ጊዜ የአገሪቱን ፖለቲካ ሲዘውር የኖረ ጨቋኝ ተብሎ ሲብጠለጠል የእኛ አገሩን የአማራ ብሔር ይመስላል፡፡ የበርማ ብሔር ሃይማኖት ተብሎ የሚወሰደው ቡድሂዝምም በአገሪቱ የጨቋኞች ሃይማኖት ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህም የኦርቶዶክስን ሃይማኖት ከአማራው ጋር ከሚያጣብቀው ደመነፍሳዊ ፍረጃ ጋር ይጎዳኛል፡፡

ሆኖም በሁለቱ አገሮች የብሔር ፖለቲካ ውዝግብ መሀከል መጠነኛ ልዩነት አለ፡፡ ሕወሓት መራሹ መንግሥት ‹‹በአማሮች የሚዘወረውን የነፍጠኛ ሥርዓት ጉልበት ለማዛል ታግየ አማራውንና የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዩን ትምክህተኛ ቡድን ከሥልጣን አርቄ ቀበርኩ›› ባይ ነው፡፡ በበርማ ያለው ደግሞ የዚህ ግልባጭ ነው፡፡ የበርማው ወታደራዊ መንግሥት እ.ኤ.አ. በ1947 በሳንሱቺ አባት ዘመን ተከብሮ የነበረውን የሕዳጣን (ማይኖሪቲ) ብሔሮች የራስን በራስ የማስተዳደር መብት ቀምቶ የጨቋኙን ብሔር (በርማን) ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ የበላይነት የሚያስጠብቅ አድሃሪ ተብሎ ይወቀሳል፡፡ ስለዚህም ሕዳጣን ብሔረሰቦች መብታቸውን ለማስከበር በሰሜን በርማ የትጥቅ ትግል ያደርጋሉ፣ ብረት ማንገቱን ያልፈለጉ ደግሞ አገር ጥለው ይሰደዳሉ፡፡ ከትቂት ወራት በፊት በሚያሳዝን ሁኔታ አገር ጥለው ሕይወትን አደጋ ላይ በሚጥል ሁኔታ በባህር ጉዞ የተዳከሙ የበርማ ዜጎች እጣ ፋንታ በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ መነገሪያ ሆኖ ነበር፡፡ ወታደራዊው መንግሥት ቡድሂዝምን በማስፋፋት እስልምናን የሚያዳክም ነው በሚልም ይብጠለጠላል፡፡ ምክንያቱ ተመሳሳይ ባይሆንም የአገራችን መንግሥትም በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ጋር እንደሚነታረክ ይታወቃል - ሌላ ተመሳስሎሽ፡፡

ሁለቱም አገራት በሴት መሪዎች የሚመሩ ዋነኛ ተቃዋሚ ፓርቲ ያላቸው መሆኑና ሁለቱ ሴቶች ከባድ እንግልት ያስተናገዱ መሆናቸውም ሌላ ተመሳስሎሽ ነው፡፡ ምንም እንኳ የበርማዋ ሳንሱቺ በጽናታቸው የቀጠሉ ቢሆን ከእርሳቸው በርታ ያለ እንግልት ያስተናገደችው የእኛዋ ብርቱካን ሚደቅሳ ጉልበቷ ተፈቶ በዋና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ቀርቶ በአገራችን ላይ ያንዣበበውን ታላቅ የችጋር መከራ በተመለከተ እንኳን አስተያየት መስጠት አቅም አጥታለች፡፡



**የሳንሱቺ ፓርቲ መንግሥት ሊያስመሠርት የሚችልበትን ድምጽ አግኝቷል ቢባልም ያሸነፈው ወታደራዊ ደጀን ያለውን የወታደራዊው መንግሥት የሲቪል ክንፍ ከሆነውን ‹‹Union Solidarity and Development Party›› (USDP) እንጂ በአገሪቱ በሰፊው የተዘረጋውን የወታደራዊውን መንግሥት ክንድ አይደለም**

## የፕራይቬታይዜሽን ‹‹ስጦታ››

አሁን በሥልጣን ላይ ያሉት የበርማ ወታደሮች ሲቪላዊውን መንግሥት በመፈንቅለ መንግሥት ገልብጠው ረዥም የሥልጣን ዘመን ያስቆጠሩ ናቸው፡፡ በአገራችንም በመፈንቅለ መንግሥት ባይሆንም ዘውዳዊውን አስተዳደር ገልብጠው ሥልጣን ላይ የወጡ ወታደሮች አገራችንን ዐሥራ ሰባት ዓመት እንዳስተዳደሩ ይታወቃል፡፡ የእኛዎቹ ወታደሮች የሥልጣኑ ዕድሜ እንደ በርማዎቹ ባይበረክትላቸውም የሁለቱም ወታደሮች አስተዳደራዊ ዘይቤ ‹‹ሶሻሊዝም መመሪያየ ነው›› በማለቱ ይመሳሳላል፡፡ ስለሆነም በቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን የሁለቱም አገራት ወታደሮች የአገሮቻቸውን የማምረቻ መሣሪያዎች ሁሉ ከግለሰብ ወደ መንግሥት የማሸጋገር ፖሊሲን (ናሽናላይዜሽን) ተግባራዊ አድርገው ነበር፡፡

የአገራችን ወታደራዊ መንግሥት ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም ጋር የሥልጣን እህል ውኃው ሲያልቅ የበርማ ወታደራዊ መንግሥት አሁንም በመንበሩ ላይ ይገኛል፡፡ የቀዝቃዛውን ጦርነት ማክተም ተከትሎ የበርማ ወታደራዊ መንግስት አሰላለፉን ከአሸናፊው የምዕራባዊያን የሊብራሊዝም ርዕዮት ጋር አስተካክሎ ቀድሞ በናሽናላይዜሽን ለመንግሥት አስተላልፎ የነበረውን የማምረቻ መሣሪያ ባለቤትነት በፕራይቬታይዜሽን የግለሰብ ይዞታ ወደማድረግ ተሻገረ፡፡ የፕራይቬታይዜሽን ፖሊሲው አፈጻጸም እጅግ ብልሹ አሠራርን የተከተለ፣ የአገሪቱን ፖለቲካ የሚዘውሩ ወታደራዊ መኳንንትን ከነዘርማንዘራቸው የሀብት ማማላይ ያወጣ፣ አሁን በአገሪቱ ለተንሰራፋው መንግሥታዊ ሙስና የማዕዘን ራስ የሆነ ነው፡፡ ሶሻሊስት ነኝ ባለበት ወቅት በወታደራዊው መንግሥት ቁጥጥር ሥር የነበሩ ዋነኛ የአገሪቱን ሀብቶች ወደ ግል ንብረትነት በመለወጡ የፕራይቬታይዜሽን እርምጃ የአገሪቱ አንጡራ ሀብቶች፣ አትራፊ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ዘርፎች ሁሉ በወታደራዊው መንግሥት መኮንኖችና ዘርማንዘራቸው እጅ ገብተዋል፡፡

የከበሩ ማዕድኖች ቁፋሮ፣ የትራንስፖርት፣ የጨርቃጨርቅ፣ የመጠጥ፣ የትንባሆ፣ የባንክ ኢንዱስትሪዎች፣ የተማሪ መማሪያ መጻሕፍት ሕትመት ቢዝነስ (ከሜጋ ጋር ይመሳሰላል) ሳይቀር የወታደራዊው መንግሥት ባለሥልጣናት ከነዘመዶቻቸውና ሸሪኮቻቸው በግል ወይም በጋራ የተቆጣጠሯቸው መስኮች ናቸው፡፡ በዚህ ሁኔታ የበርማ ወታደራዊ ባለሥልጣናት የማይገናኙትን ወታደርነትና የባለጠግነት እጅግ ቅንጡ ሕይወት አጣምረው ይዘዋል፤ ለተጠጋቸውም ሁሉ ከባለጠግነታቸው ያረሰርሳሉ፡፡

በአገራችን ደርግን ጥሎ ሥልጣን የያዘው ኢሕአዴግ ወደ ሥልጣን እንደመጣ ሶሻሊስትነቱን በአእምሮው ጓዳ አስቀምጦ ከአሸናፊው የምዕራባዊኑ ዴሞክራሲያዊ ዘይቤ ጋር ራሱን አሰልፏል፡፡ የምዕራቡ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ዘይቤ ዋና የሆነውን የፕራይቬታይዜሽን ፖሊሲን መተግበርንም ለምዕራባዊያኑ የመለወጡ እማኝ አድርጎ እንደማቅረብ ወስዶት ነበር፡፡ በአገራችን በኢሕአዴግ የተደረገው የፕራይቬታይዜሽን አተገባበር የሕወሓት መራሹን መንግሥት ባለሥልጣናት ዘር ሀረጎች እና ጋሻ ጃግሬዎች ደርሶ ባለጠጋ የማድረጉ ረዥም ጉዞ መሠረት እንደነበር ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ ወየሳ ‹‹ከሆቴሉ በስተጀርባ›› በሚል ርእስ የጣይቱ ሆቴልን መቃጠል አስመልክቶ በጻፈው አንድ ግሩም ጽሑፍ ያስረዳል፡፡

## ወታደራዊ አፋራምነት

የሁለቱ አገራት መንግሥታት ለምርጫ ሽንፈታቸው የሚያሳዩት ምላሽ ተመሳስሎሻቸውን ያንረዋል፡፡ የበርማው ወታደራዊ መንግሥት እ.ኤ.አ. 1990 አገሪቱ የተደረገውን ብሔራዊ ምርጫ ነጻና ፍትሐዊ ለማድረግ ቆርጫለሁ ብሎ ደፋ ቀና ማለት ያዘ፡፡ የፖለቲካ ሜዳውን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ክፍት አድርጎ ምቹ ሊባል የሚችል የውድድር ሜዳ ከፈተ፡፡ሳን ሱቺ የሚመሩት ‹‹National League for Democracy›› (NLD) የተባለው ፓርቲ ወታደሮቹን ከኖሩበት የሥልጣን መንበር ሊገፈትር የሚችል አብላጫ ድምጽ አገኙ፡፡ ይሄኔ ወታደሮቹ አፈሩ፤ የዋነኛውን ተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ሳንሱቺን ለቁም እስር የአገሪቱን ዴሞክራሲያዊ ሂደት ደግሞ ለኢልሽ ጉዞ ዳረጋቸው፡፡ በ1997ቱ የአገራችን ታሪካዊ ምርጫ የተደረገወም ይሄው ነው፡፡ ተቃማዊዎች እግር እስኪያወጡ ጠብቀን እግራችን እንቆርጣለን ያለውን ቃል ተግባራዊ ያደረገው ኢሕአዴግ ከበርማዎቹ የሚለየው የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን ለቃቅሞ በአስቀያሚው ቃሊቲ እስር ቤት ማጎሩ ነው፡፡ የኢሕአዴግ የፖለቲካ መንትያዎቹ የበርማ ወታደራዊ አምባገነን ገዥዎች በተወሰነ መልኩ ተሻይ ናቸውና በቤት ውስጥ ቁም እስር ምረዋቸዋል፡፡ ዕድሜ የተጫናቸውን የተከበሩ አዛውንቶች በሰደፍ እየነረተ ቃሊቲ እስር ቤት ከሚከረችመው ኢሕአዴግ ጋር ሲነጻጸር በርማዎቹ የቤት ውስጥ እስር እንደ ድሎት ሊቆጠር ይችላል፡፡

ተቃዋሚዎቻቸውን በእስር ከርችመው ስለብቸኛ መድህንነታቸው የሚያወሩት ሁለቱ መንትያ አምባገነነኖች ከዚህ ሁሉ በኋላም ስለዴሞክራትነታቸው ይዘምራሉ፡፡ ተቃዋሚያቸውን ጸጥ ያደረጉት በርማዎች ዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሚያካሂዱበትን ባለ ሰባት ነጥብ ዕቅድ ነደፉ፡፡ ምርጫውም እ.ኤ.አ. 2010 ተደረገ፡፡ ሂደቱም ሆነ ውጤቱ ግን ‹‹ወታደር ወታደርነቱን ነበር ኾርጉርጉርነቱን አይስትም›› የሚሉት ዓይነት ሆነ፡፡ የሳንሱቺ NLD ፓርቲም ከምርጫው ራሱን አገለለ፡፡ ይሉኝታ ቢሱ ወታደርዊ መንግሥት 80 በመቶ የምርጫ ድምጽ አገኘሁ፤ ይህም ስለዴሞክራሲ የመልፋቴ ምልክት ነው ሲል አከለ፡፡ በ1990 ምርጫ መሪዎቹን በቤት ውስጥ በማሰር የታለፈው ፓርቲ በዚህኛው ምርጫ በአገሪቱ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ በሕግ ታገደ፡፡ መሪዋ ሳንሱቺም ለሁለት ዐሥርታት ዘመን ያህል በቤት ውስጥ እስራቸው እንዲቆዝሙ ተደረገ፡፡ የዚህን ቅጅ በኛ አገርም አናጣውም፡፡ በሦስተኛው አገራዊ ምርጫ በከፍተኛ የሽንፈት ለበቅ የተገረፈው ኢሕአዴግ እውነተኛ ተቃዋሚዎቹን ‹‹ነውጠኛ›› የእርሱን እንጎቻዎች ደግሞ ‹‹ለዘብተኛ›› በሚል ከፋፍሎ ነውጠኛ ያላቸውን ከፖለቲካው መዝገብ ሲሰርዝ መሪዎቹም ‹‹በነፍጥ እንሚከር›› ሲሉ ዱር ቤቴ አሉ፤ መንግሥትም ‹‹ነውጠኝነታቸውን›› ወደ ‹‹አሸባሪነት›› አሳድጎ ስማቸው እንኳን በአገር ውስጥ ጮክ ተብሎ እንዳይጠራ የሚከለክል ዓይነት ሕግ አወጣ፤ የአገሪቱ ፖለቲካም መስህብ የለሽ ፍዝ ሆኖ አረፈው፡፡ ጠብ መንጃን ‹‹ከሕግ›› እና ፕሮፖጋንዳ ጋር ባዋደደ መንገድ የሰላማዊ ተቃዋሚውን ጎራ ጭር ያደረገው ኢሕአዴግ በቀጣዩ የ2002 ምርጫ ብቻውን ወደ መወዳደሪያ ገብቶ ‹‹99.6 በመቶ የፓርላማ ወንበር አሸነፍኩ፤ ይህም የመድበለ ፓርቲ ስርዓት ማበብ የዴሞክራሲ መጎምራት ምክት ነው›› ሲል ዓይኑን ሳያራግብ ነው፡፡

የሁለቱ አገሮች ተመሳሳይ አምባገነኖች ተቃዋሚን ጸጥ የማስደረጉ እርምጃ የተቃዋሚዎችን ለሁለት ከፍሎ ጉልበታቸው እንዲዝል ሆኗል፡፡ ተቃዋሚዎቹ ነፍጥ ወደ ማንሳት አለያም በዛው በሰላማዊ ትግል መፍገምገሙ ያዋጣል በሚል ለሁለት ተከፍለዋል፡፡ ይህ ክፍፍል የተቃውሞውን ጎራ ድካም አበርትቶ፣ ተስፋ የማይጣልበት እያደረገው ነው ይላሉ ፕ/ር መሳይ ከበደ ሰሞኑን ‹‹Dictatorship and its Evolution›› በሚል ርእስ በጻፉት ጽሑፍ፡፡ የተቃዋሚው ጎራ መዳከም ደግሞ ዴሞክራሲን በማሳደግ በኩል መንግሥት አንዳች ለውጥ እንዲያመጣ ለማስገደድ የማይችሉ አድርጓቸዋል ሲሉ ያክላሉ ፕ/ር መሳይ ከበደ፡፡

## ዘ-ፀአት ለዴሞክራሲ

ከላይ በትቂቱ ለማሳየት እንደተሞከረው የበርማ ፖለቲካ ከአገራችን ፖለቲካ ጋር በእጅጉ የሚመሳሰል ሆኖ ኖሯል፡፡ ሆኖም በቅርቡ በርማ የለውጥን መልካም ዕድል እየመረጠች ትመስላለች፡፡ እናም ለውጥ የሚቀርበው ከማይመስለው የአገራችን ፖለቲካ ጋር የሚኖራት ተመሳስሎሽ እየቀነሰ እንደሚሄድ ይገመታል፡፡ በርግጥ በርማ ከአገራችን መለየት የጀመረችው እ.ኤ.አ. በ2011 ለውጥ ፈላጊነታቸው የሚነገርላቸው የቀድሞው ጀነራል ጊን ሲን የአገሪቱ ፕሬዚደንት እንዲሆኑ ከሆነ በኋላ ነው፡፡ ሰውየው ወደ ሥልጣን በመጡ ማግሥት መለዮ ለባሹ ቀፍድዶ

ወደ ገፅ 10 ዞሯል



## የዜጎች ድምጽ

(በዚህ ዐምድ ኢትዮጵያውያን የማኅበራዊ ድረ ገጽ ተጠቃሚዎችን የሚያወያዩና የሚያከራክሩ አንኳር ጉዳዮች ተመርጠው ይቀርባሉ)

በዕውቀቱ ስዩም

# "ገጽታ ግንባታ?"

በአገራችን አብዛኛው ዜጋ ለቀን ጉርስና ላመት ልብስ ሲታገል የሚኖር ነው፡፡ ጌቶች ደግሞ አማርጠው ይበላሉ፤ አማርጠው ይለብሳሉ፤ በለስ ሲቀናቸው ደግሞ የሃያ አምስት ሚሊዮን ብር ቪላ ይቀልሳሉ፡፡ እንዲያም ሆኖ ደግሞ መከበርና መደነቅ ይፈልጋሉ፡፡ ሰው ምንም በስጋው ቢመቸው በሌላው ተመዝኖ እንደቀለለ ሲሰማው ደስተኛ አይሆንም፡፡ ስለዚህ ጌቶች ያስንቀናል ብለው የሚያስቡትን ነገር በሙሉ ጠምደው ይይዙታል፤ ይዋጉታል፡፡ ኢትዮጵያ- ጌቶች ለኩራታቸው፤ ዜጎች ለራታቸው የሚታገሉባት መድረክ ናት፡፡

ብዙ ጊዜ ረኀብ ሲከሰት ጌቶች ረኀብተኛውን ሁሉ ሰብስበው ጎተራ ውስጥ ሊደብቁት ይቃጣቸዋል፡፡ የድሆች የተራቆተ ሰውነት የገጠጠ አጥንት፤ የጌቶችን የመከበር ፍላጎት ያከሽፈዋል፡፡ ባንድ ወቅት በቦሌ መድኃኒዓለም ዳርቻ ስራመድ አካባቢው አለወትሮው በለማኞች አለመሞላቱን ታዝቤ ተገረምሁ፡፡ ያዲሳባ አስተዳደር፤ ለማኞችን ‹‹በጥቃቅንና አነስተኛ›› አደራጅቶ ያሳለፈላቸው መስሎኝ ነበር፡፡ እንደተሳሳትሁ ለመረዳት ጥቂት ደቂቃ በቦታው መቆም ነበረብኝ፡፡ አንዲት ተመጽዋች ሴት ልጇን ይዛ ከቅጽሩ ሥር ለመቀመጥ ስታነጥፍ ፖሊስ በቆረጣ ገብቶ ‹‹ዞር በይ ነግሬሻለሁ›› እያለ ሲያዋክባት ተመለከትሁ፡፡ የደነገጠ ልጇን እየጎተተች ተወገደች፡፡ ከዚያ ወዲያ ከአቡነ ጳውሎስ ሐውልት በቀር በአካባቢው ደፍሮ የቆመ አልነበረም፡፡ ወደ ቤቴ ከመሄዴ በፊት ያቡኑን ወፍራም ሐውልት ዞር ብየ ሾፍኩት፡፡ እጁን እንደ ራስ ኃይሉ ሙርጥ ገትሮ ከፊት ለፊት ያለውን ‹‹ሬድዋን ሕንጻ›› ሲባርክ ነበር፡፡

‹‹ገጽታ ግንባታ?››

በዘመናችን የተራቡ ዜጎችን መደበቅ እንደ ገጽታ ግንባታ የሚቆጥሩ ሰዎችን ከባለሻሽ ሌቦች ለይቼ አላያቸውም፡፡ በነገራችን ላይ፤ ብርቱካን ዓሊ ግለሂስ ያደረገችበትን ዘገባ ካየሁ በኋላ ለጊዜው ለመናደድ እንኳ ቸግሮኝ ነበር

በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን የፍርድ ሚኒስትር የነበሩት አፈ ንጉሥ ነሲቡ የሌባ ብዛት ቢያስቸግራቸው አንድ መላ መቱ፡፡ ሲሰርቅ የተገኘ ወሮበላ ግንባሩ ላይ በጋለ ስለት ምልክት እንዲደረግበት ደነገጉ፡፡ ታድያ ሌቦች የዋዛ ስላልነበሩ ሻሽ በመጠምጠም የግንባራቸውን ጠባሳ ሊሰውሩት ሞክረዋል፡፡ በጊዜው ደግሞ ሻሽ መጠምጠም ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የወረደ የነገሥታቱና የመሳፍንቱ ወግ ነበር፡፡ ጮሌ ሌቦች ውርደታቸውን ከመሸፈን አልፈው የንጉሥ ገጽታ ተላብሰው ብቅ አሉ፡፡

በዘመናችን የተራቡ ዜጎችን መደበቅ እንደ ገጽታ ግንባታ የሚቆጥሩ ሰዎችን ከባለሻሽ ሌቦች ለይቼ አላያቸውም፡፡ በነገራችን ላይ፤ ብርቱካን ዓሊ ግለሂስ ያደረገችበትን ዘገባ ካየሁ በኋላ ለጊዜው ለመናደድ እንኳ ቸግሮኝ ነበር፡፡ ዘገባውን የሠራው ጋዜጠኛ እንዲህ ዓይነቱን ካንድ ድንጋይ የተጠረበ ደደብነት ተሸክሞ የመኖር ችሎታው በጣም አስደነቀኝ፡፡ በዚህ በሰላቢው ቀን ይቅርና፤ በደህናው ቀን እንኳ የባላገሩን ራብና መከራ ከጉያው የበቀልን ልጆቹ እናውቀዋለን፡፡ ዐሥራ አምስት ሚሊዮን ሕዝብ መደበቅ ሰማይን በመዳፍ ለመሸሸግ እንደ መሞከር ይቆጠራል፡፡ መፍትሔው በተቸገሩ ሰዎች ጫማ ቆሞ ነገሮችን መመልከት ነው፡፡ ለነገሩ ችግርን ያልቀመሰ ሰው ለችግረኛ መራራት እንዴት ይቻለዋል? አብን ተውትና፤ ንገሩት ለወልድ ተገርፏል ተሰቅሏል፤ እሱ ያውቃል ፍርድ እንዲል ባላገር፡፡


ኮከብ ብርሃን
የባህል ሕክምና ማዕከል

ማንኛውም ባለጉዳይ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በትህትና በማስተናገድ ሳይ ሲሆኑ በአሁኑ ሰዓት ትክክለኛ ፈውስ የተገኘላቸው በሽታዎች በከፊል፡-

- ለሆድ ሕመም
- ለእጅና ለእግር ቁርጥማት
- ለአስም
- ለሾተላይ
- ለራስ ሕመም
- ለእግር ፈንገስ
- ለሚጥል በሽታ
- ለማዲያት
- እጁን ለሚጠባ
- ለትምህርት
- ለእጅ ሰብእ
- ለጭርት ወይም ማሳከክ
- ለአይነ ጥላ
- ለወር አበባ መብዛት
- ሌሊት ለሚሸና

በተለይ የብዙ ሰዎችን ችግር የሆነውን የስንፈተ ወሲብ /በመቀባት/ ብቻ ፈውስ ይሰጣል።

አድራሻ፡-
ሐና ማርያም ቀለበት መንገድ ንግድ ባንክ ፊት ለፊት
ለበለጠ መረጃ፡- 0911 808241 /0913 778746/ 0912 635069
በእውነት ስለ እውነት እንተጋለን!!


## መርዝን በማር ለውሶ . . .

የማቋቋም እንዲሁም በክልልም ሆነ በፌደራል አስተዳደሮች ውስጥ ፍትሃዊና ሚዛናዊ የሆነ ውክልና (የአመራር ሚናን ጨምሮ) የማግኘት መብት እንዳላቸው የተደነገገ ሲሆን የዩኒቨርስቲ ቦርድ ሰብሳቢነት ብሎም የዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንትነት በአንድ አካባቢ ባለ ተቋም በአካባቢው ሰው መወከሉ ሊበረታታ የሚገባው ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም በአካባቢ ልጆችም የተመሩና እየተመሩ ያሉ የመንግሥት ተቋማት እጅግ አስደናቂ አፈጻጸሞችን እንዳመጡ ማየት ችለናልና፡፡ በዚህም ዩኒቨርስቲዎች ከተቋቋሙበት የመማር ማስተማርና የምርምር ሥራዎቻቸው ባሻገር የማኅበረሰብ ሥራዎችንም እንዲሠሩ ይህም ከማኅበረሰቡ ጋር በቋንቋ ከመግባባት ጀምሮ በቅርበት የሚያውቁትን የማኅበረሰቡን ችግሮች ከመፍታትና ባህልና ቋንቋቸውን ከማሳደግ አንፃር የአካባቢው ተወላጅ ምሁራኖች በአመራር ቦታ ላይ ቢቀመጡ ሊኖራቸው ከሚገባቸው ሚና አንጻር በበጎ መልኩ የሚታይ ጉዳይ ሊሆን ይገባል፡፡

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲን ተሞክሮ ስንመለከት በእስከ ዛሬው የ28 ዓመት የዩኒቨርስቲው የጉዞ ታሪክ ውስጥ ዩኒቨርስቲውን በቁጥር 3 የሚሆኑ የጋሞጎፋ ተወላጅ ምሁራኖች ነበሩ የመሩት፡፡ እነሱም ዶ/ር ቦጋለ ገ/ማርያም (ለ2 ዓመታት)፣ ዶ/ር ንጋቱ ጫፎ (ከ2 ዓመት ላነሱ ጊዜያቶች ያውም በውክልና) እና ዶ/ር ታረቀኝ ታደሠ (ለ 4 ዓመታት) መምራታቸው የሚታወቅ ሐቅ ነው፡፡ በተጨማሪም አሁን ባለው የዩኒቨርስቲው ተጨባጭ ሁኔታ ከ90% በላይ የሆነው የዩኒቨርስቲው የአካዳሚክ አመራር ዘርፍ (ከትምህርት ክፍል እስከ ፕሬዚዳንት የኃላፊነት) ቦታዎች ከአካባቢ ተወላጆች ውጪ ባሉ የአገራችን ኢትዮጵያ ልጆች ማለትም በወንድሞቻችን እየተመሩ መገኘታቸው የጸሐፊው ጽሑፍ ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲያችን አንጻር ምን ያህል ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ዓይነት እንደሆነ ከምንም በላይ አብዛኛው የዩኒቨርስቲችን ማኅበረሰብ አካላት ይረዱታል ብዬ አምናለሁ፡፡ የራስንና ከራስ ጋር የተሳሰረን የኔትወርክ ሰንሰለት ለመጥቀም በሚመስል መልኩ የሚወሩና የሚጻፉ ጽሑፎች ቁጥራቸው ውስን የሆኑ የአካባቢው ተወላጅ ምሁራኖችን ለማሸማቀቅ፣ ከሌላው ጋር በማናደፍ የቆየ የአብሮነትና የመቻቻል ታሪካቸውን ለማበላሸትና ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቀሚነታቸውን ለመገደብ ከመሻትም በላይ በእነዚህ ውስን የአካባቢው ተወላጅ ምሁራኖች ላይ የተቃጣ የዘር ማጽዳት ዘመቻም ነው እላለሁ፡፡

በነገራችን ላይ ለጸሐፊውና ለአንዳንዶች ቢዋጥላቸውም ባይዋጥላቸውም የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ከፌደራል መንግሥት ባለፈም ለደቡብ ክልላችንም እንዲሁም ለጋሞጎፋ ሕዝቦች ድርሻቸው የሆነ ሀብታቸው እንደሆነም ሊታወቅ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ተቋሙ ከሀገራዊ ተልዕኮው ባሻገር ዘርፈ ብዙ የሆነ አካባቢያዊ ጠቀሜታም አለውና፡፡ ቢያንስ ቢያንስ በአንድ ወቅት በተቋሙ በተፈጠረ ሁከት ተማሪዎች ሕንጻዎችንና መስታወቶችን ለማውደም በተንቀሳቀሱበት ወቅት ተቋሙን ለመታደግ ቀድሞ ዘሎ የገባው በዙሪያው ያለው የአካባቢው ሕዝብ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ምንም እንኳን የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ለመንጣጣት ቢሞክርም፡፡

በእርግጥ በአሁኑ ሰዓት በርካቶች በሕይወት ዘመናቸው እንዲኖሯቸው ከሚፈልጉዋቸው ነገሮች መካከል ሥልጣን አንደኛው እንደሆነ የሚታወቅ ቢሆንም በአመዛኙ ሊባል በሚችል መልኩ አብዛኞቹ ሥልጣን ፈላጊዎች አገራቸውንና ሕዝባቸውን በአግባቡ በመምራት ለመጥቀም በማሰብ ሳይሆን በሥልጣን ውስጥ ያሉትን ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ካላቸው ክፍተኛ ፍላጎት በመነሳት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ምንም እንኳን ማንም ምንም ነገር የመፈለግ መብቱ የተጠበቀ እንደሆነ ቢታወቅም ማንም ሰው ለመሾም ካለው ከፍተኛ ፍላጎትና ጉጉት በመነሳት ብቻ ሿሚው አካል ተነስቶ ይሾመዋል ማለት አይደለምና በቅርቡ በዩኒቨርስቲያችን በተደረገቅ አገር አቀፍ ስብሰባ ወቅት የተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ «የሹመቱን የቤት ሥራ ለእኛ ተውት» ባሉት አግባብ መሠረት ሹመትን ለሚመለከተው አካል ትተን ሥራችንን በአግባቡ መሥራቱ የሚበጀን ይመስለኛል እያልኩኝ መንግሥት፣ የቦርድ አመራር አካላትና እውነታውን ከማንም በላይ የሚያውቀው አብዛኛው የዩኒቨርስቲያችን ማኅበረሰብ እነዚህን ለጥቅማቸው ብቻ ሲሉ አፍራሽ ተልዕኮን አንግበው የሚያራምዱ ጸረ ሕዝብና ሕገ መንግሥት የሆኑ ግለሰቦችና ኃይሎችን ከመጥፎ አመለካካተቻው ጀምሮ ‹‹ሃይ!›› ይሏቸው ዘንድ ጥሪዬን በአክብሮት አስተላልፋለሁ፡፡

## ልዩ ዘገባ



ሙሉቀን ተስፋው

# ሰቆቃ ወጎንደር

የጎንደር መሬት ከዝናብ እኩል የሰው ደም መጠጣት ለምዷል። ዓመት በዓል የሆነ ጊዜማ ነገር አለው። ጎዳናው ሁሉ ደም ደም ይሸታል። በቀይ ሽብር ዘመን ስንት ወጣት አለቀ? ስንት ሕዝብ መስቀል አደባባይ ላይ ታነቀ? የሚረሸኑ ወጣቶች ደም ስንት ኪሎ ሜትር ተጓዘ?

የመንግሥት መለወጥ የጎንደር መንገዶችን በሰው ደም ከመጨቅዬት አልለወጣቸውም። የደርግ መሄድ የኢሕአደግ መምጣት የሰዎችን በግፍ መገደል አልቀነሰውም፤ አላቆመውም። በደርግ ዘመን ሰው በአዘቦት ቀን ይሞት ነበር፤ በኢሕአዴግ ሁልጊዜም ቢኖርም በዓመት በዓል እለት ይብስበታል። በደርግ በአደባባይ ይሰቀላል፤ በኢሕአዴግ በቤተ መቅደስ የክርስቶስ ስጋና ደም በሚፈተትበት ቦታ ለማንም ሥርየት ያልሆነው የጎንደሬዎች ደም ይፈሳል። የሚሞቱ ሰዎች ደም ለቀሪዎቹ ሥርየት ቢሆን ኖሮ በጎንደር የተሰው ንጹሐን ሰዎች ደም ለኢትዮጵያውያን ሳይሆን ለዓለም ልጆች ሁሉ ቤዛ መሆን በቻለ ነበር። በጎንደር የሰው ልጆች ደም በቅዱሱ ሥፍራም ሆነ በ‹ወንጀለኞች› መታጎሪያ፣ በቤትም ሆነ በአደባባይ፣ በጫካም ሆነ በከተማ ይፈሳል፤ ግን ማንም ቤዛ መሆን አልቻለም። በጎንደር ዘመናት አልፈው ዘመናት ሲመጡ የትናቱን ተመስገን የሚያስብል ‹አጃኢብ› የተባለለት ግድያ አለ። በምድር የተሰው ሰዎች ደም ሁሌም ይጮኻል! የፍትሕ ያለህ ይላል! የጎንደር እናቶች እንባቸውን ከራሔል እንባ በላይ ከፍ አድርገው ረጭተውታል! ኤሎሄ አሎሄ!

የ1986 ዓመተ ምህረትን የዘመን መለወጫ የሚጠባበቁ ዜጎች አዲሱን ዓመት የፍስሃና የአዱኛ ያደርግላቸው ዘንድ ምኞታቸው ነበር። የጎንደር ሕዝብ ለአርባ አራቱ ታቦታት ምህላውን ያሰማ ነበር። ነሐሴ አለቀ፤ ጳጉሜ ገባች። ‹እዮሃ አበባየ› ሊባል ቀናት ቀሩት። ግን የጎንደርን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላ ኢትዮጵያውያን ያሳዘነ፣ ስለ ፍትህ ያስጮኸ፣ የቤተ መቅደስ ደጆች የተደፈሩበት አትሮንሱ ሥር፣ አውደ ምህረት ላይ አስከሬን ተደረደረ። የመንግሥት ኮማንዶዎች 65 የሚሆኑ ነፍሳትን በርእሰ አድባራት አደባባይ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ደፏቸው። ቤተ መቅደስ ተደፈረ፤ በቃ ጎንደር አነባች። ጊዜ ቀጠለ … ፍትሕ ከሰማይ ራቀች። ከዚያን ዘመን ጀምሮ በቡድንም በተናጠልም ሰው ይሞታል። ቤታቸው በግሪደር የፈረሰባቸው ሰዎች ለምን ሲሉ ማስፈራሪያቸው ነፍጥ ነው። አገር አማን ብለው ጥምቀት ለማክበር የሚሄዱ ሰዎች በመኪና ውስጥ በእሳት ተቃጥለዋል። በአርማጭሆ፣ በጭልጋ፣ በቋራ፣ በጸለምት፣ በወልቃይት፣ በጋይንት ወዘተ. ሁሉ በአንድም በሌላም ደም ፈሷል። ጋብ ያለ እየመሰለ በዘመናት መካከል የሰው ደም ይፈሳል።

ለመግቢያ ያክል ይህን ካልኩ ወደ ሰሞነኛው ጉዳይ ልግባ። ሕዳር 21 ቀን 2008 ዓ.ም. የጎንደር ሕዝብ ዓመታዊውን የቅድስት ማርያም በአል ያከብራል። ምዕመኑ ከሎዛ ማርያም እስከ ግምጃ ቤት ማርያም ድረስ ባሉ የማርያም አብያተ ክርስቲያናት ሲነጉድ አርፍዷል። ጸአዳ በለበሰ ምዕመን ጎንደር ነጭ በነጭ ሆና አርፍዳለች። እኩለ ቀን ሆነ፤ ካህናት ወደ ቅዳሴ ገቡ። በምሳ ሰዓት የታሰረ የሚጠይቀው ደግሞ ወደ በአታ ማረሚያ ቤት ሄደ። በግምት ከ7፡00 እስከ 7፡30 ቢሆን ነው። የሚጠይቁ ሰዎች ውስጥ እያሉ የማረሚያ ቤቱ ‹መንስ ቤት› (ምግብ የሚዘጋጅበት ቤት) ቃጠሎ ተነሳ። የጥበቃ ፖሊሶች ዝግጁ አልነበሩም። በከተማው በቂ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መኪና የለም፤ ከአየር ማረፊያ የመጣውም ቢሆን አደጋውን ለመቀነስ የሚችል አልነበረም። እሳቱ የተነሳው የወንዶች መኖሪያ ጋር በመሆኑ ታሳሪዎች ‹‹ከአደጋው ታደጉን›› የሚል ጥሪ አቀረቡ። በጀርባ እሳት አለ፤ በፊት ለፊት ደግሞ ጥይት ተደግኗል። የበአታ ማረሚያ ቤት ማኅበረሰብ ከ3000 ይበልጣል። ቀውጢ ሆነ፤ ጩኸቱ በዛ። ቅዳሜም ሆነ አራዳ ገበያ ከማረሚያ ቤቱ ሩቅ አይደለም። ኅብረተሰቡ ከእሳት አድኗቸው የሚል ጥያቄ አቀረበ። ብዙ ታራሚዎች አጥር እየዘለሉ ወደ ሕዝቡ ተቀላቀሉ። ከፊሎች ሲዘሉ መትረጊስ ቀደማቸው። ሰው በሰው ላይ አስከሬን በአስከሬን ላይ ተነባበረ። በሙታ በሙታን ላይ፣ ሙታን በሕያዋን ላይ ወዳደቁ። ሰቆቃው ያኔ ነው የጀመረው። በሰዓቱ አንዲት ከአምስት ዓመት በታች የሆነች ሕጻን ይዛ እስረኛ ለመጠየቅ የገባች እናት ከፊቷ የሚወዳድቁ ሙታንን ስትመለከት ሕሊናዋን ሳተች፤ ልጅ መያዟንም ረሳች።

በደመነፍስ ወደሚተኩሱት ወታሮች እየሮጠች እንዲያድኗቸው ተመጸነች። የሙታን ደም ባጨቀየው መሬት ላይ በሰደፍ ተመታ ወደቀች። ውስጥ ልጆቻቸው፤ ባሎቻቸውና ዘመዶቻቸው የታሰሩባቸው እናቶች ዋይታ በጽሑፍ የሚገለጽ አይደለም፤ እናቶች መቀነታቸውን አጥብቀው በሲቃ አስፓልት ላይ ሲንከባለሉ ማየት እንዴት ባለ ቋንቋ መግለጽ ይቻላል? ‹‹ወይኔ ልጄ! ወይኔ አባቴ! ወይኔ ወንድሜ! ወይኔ ጓዴ!›› የሚሉ ድምጾች ትናጋ እስኪሰነጠቅ ድረስ በዚያም በዚህም ይሰሙ ነበር። የተሰባሰበው ሕዝብ እስረኞች በእሳት እንዳያልቁ አጥብቆ ተመጸነ፤ አልሆነም፤ በየቦታው ሲንቀሳቀስ የነበረ ሰው ድፍት ይል ጀመር። ሕያው አካል በሰኮንድ ግዑዝ በድን ሲሆን ይታያል። ወጣቶች ስሜታቸውን መቆጣጠር አቃታቸው። ድንጋይ መወራወር ተጀመረ። የፖሊስ ጥይት ዒላማው የሰው ልጅ ደረትና ጭንቅላት ሆነ። እስረኞች የሚሞቱት እየሞቱ በእሳት ከመበላት ጥይት ይሻላል በሚል ስሜት ከመትረጊስ ጥይት ጋር እሽቅድድም ጀመሩ። በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገርኩት አንድ ወጣት ‹‹ምርጫው እኮ በእሳት ወይስ በጥይት መሞት የሚለው ነው፤ የትኛው ያስቃያል?›› ሲል መልሶልኛል።

ከእሳቱ ለማምለጥ የከመትረጊስ ጋር የሚታገሉ እስረኞች ቁጥር ሲጨምር ፖሊሶች መሣሪያቸውን ታጥቀው ከግለሰቦች ቤት ጣሪያ ላይ በውጣት አነጣጥረው መግደል ጀመሩ። የሚሞት አስከሬን ወደ ግቢው ነው የሚሸከፈው። አንዳንድ ፖሊሶች የሚሮጡ ታራሚዎችን ተከትለው በመሄድ እነርሱን ሲያጡ ያገኙትን ንጹህ ዜጋ ገድለው ይጎትቱም ነበር። አንድ ታራሚን ለመያዝ የሁለት ሕጻናት ጭንቅላት በጥይት ፈርሷል። አንድ ፖሊስ አንድ እስረኛን እየተከተለ ቅዳሜ ገበያ ላይ ሲደርስ ጠፋው፤ እዚያ አካባቢ ትንሽቱ መስጊድ አጠገብ ኳስ የሚጫወቱ ሦስት ልጆችን አገኘ። ኳስ በእጁ የያዘውን ልጅ ግንባሩን አለው በጥይት። መቼም በዚህ ጊዜ ሕጻኑ እስረኛ መስሎኝ ነው አይባልም?

አንድ አዛውንት ባጃጅ ውስጥ እንዳሉ የፌደራል ፖሊስ ዒላማ ሰላባ ሆነው ተዘረገፉ። ‹ፍቅር› እሚባል ካፌ ፎቅ ላይ ሻይ ሲጠጡ የነበረ ጎልማሳ ድፍት እንዳለ ነው የቀረው። የመኪናውን ጎማ ሲፈትሽ የነበረ ረዳት ቀበሌ 9 ከተጎነበሰበት ቀና ሳይል ቀረ። የሚሞቱ ሰዎች በሙሉ ወደ ማረሚያ ቤቱ ነበር አስከሬናቸው የሚወሰደው። ሕዝቡ ላይ ህጻን አዋቂ ሳይሉ ጥይትና የመርዝ ጋዝ በጅምላ አርከፈከፉ። የአቡን ጎርጎሪዮስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሰርቪስ አካባቢው ደርሰው ነበር። ሕጻናቱን የመርዝ ጋዝ ተረጭቶባው መኪና ውስጥ ሁሉም ወደቁ። ውኃ እየተደፋባቸው ነው መንቃት የቻሉት።

የሕግ ታራሚዎች በምንም ይሁን በምን ከፖሊስ ፊት ከተገኙ መሞታቸው ቢያንስ ግን በጥይት እግራቸው መመታቱ ግዴታ ይመስል ነበር። ጻዲቁ ዮሐንስ አካባቢ በጭንቀት ያገኘዋት ልጅ በእንባ እየታጠበች ‹‹እኔ ሰው ሲሞት አይቼ አላውቅም። ጥይት እየጮኸ ሦስት ሰዎች በድንገት ደረሱ። አንደኛው ‹እባክሽ ፎጣ ስጭኝ› አለኝ። እኔም በድንጋጤ እምቢ አልኩት። ቀና ስል ሦስቱም ሕልም በሚመስል መልኩ ወድቀዋል። ሁለቱ እግራቸውን ነው የተመቱት፤ ፎጣ የጠየቀኝ ልጅ ግን ከአንገቱ ሥር ደም ሲወጣ ቀና ብሎ መልሶ ከንበል አለ›› በማለት በጭንቀት ውስጥ ሆና ነው የነገረችኝ። ሕዳር 21 ቀን ጎንደር ላይ ሞት ነግሦ ዋለ። የተጠራቀሙ አስከሬኖች ወደ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል - ቸቸላ - ተወሰዱ።

በዚህ ቀን የሞቱ ሰዎችን በተመለከተ ያለው ዳታ የተለያየ ነው። የሞቱ ሰዎች ከማረሚያ ቤቱ አምልጠዋል የተባለበት አጋጣሚ ሁሉ አለ። ወደ ሆስፒታል የተወሰዱ አስከሬኖች 22 እንደሆኑ ነው ከተለያዩ ምንጮች ያረጋገጥኩት። ሆኖም በጊዜው በሰዓቱ አካባቢው የነበሩ ሰዎች ሳነጋገር ብዙዎቹ የሕግ ታራሚ ብቻ 38 ሰው ሞቷል ብለዋል። ከውጭ ያሉ ንጹሐን ሰዎችን ጨምሮ ሕዳር 21 ቀን የሞቱ ሰዎች ከ45 ይበልጣል ይላሉ ያነጋገርኳቸው ብዙ ሰዎች። ከፖሊስና ከከንቲባ ጽሕፈት ቤት ለማረጋገጥ ያደረግኩት ሁሉ ስኬታማ አይደለም። ሆኖም አንድ ስሙ እንዳይጠቀስ የፈለገ የፖሊስ አባል በውል ማወቅ ቢከብድም ከ22 በላይ ሰዎች መሞታቸውን ነው የተናገረው። ሆስፒታል ረቡዕ ዕለት ዝግ ቢሆንም ሐሙስ በጠዋት ግን ከገቡ በኋላ የሞቱ ሰዎችን ስም ዝርዝር ለጥፈው ነበር።

የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ግን 16 ሰው ብቻ ተረጋግጦ ሞቷል ሲል እንደዘገበ ሰምቻለሁ። ይህ አይነት ሽፍጥ አዲስ አይደለም። አደባባይ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በ86 ዓ.ም. አዲስ ዓመት ዋዜማ የተረፈረፉትን ንጹሐን ሰዎች በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ከንቲባ ጽሕፈት ቤቱን ሊዘርፉ የሞከሩ የቀድሞው ሠራዊት አባላት በቁጥጥር ሥር ውለዋል በማለት ከዘገበ ከ22 ዓመት በኋላ ኢሕአዴግ ያንኑ ውሸት ዛሬ ደገመው።



ከውጭ በጠያቂና በፖሊስ ከውስጥ በታራሚና በፖሊስ መካከል ግጭት ተከሰተ። ግቢ ውስጥ ያለው እሳር ተቃጠለ። ከውጭ በኩል የሄደው ጠያቂ መትረጊስ ሲጮኽበት በድንጋይ መመለስ እንደማይችል በመገንዘብ ተበተነ። ውስጥ ያሉት ግን ከመረሸን አላመለጡም። እነሆ ሐሙስ ሕዳር 23 ቀን የተጨማሪ ሰዎች ደም ፈሰሰ

ቀደም ባሉ ቀናት በብር ዋስ እንዲፈቱ ፍርድ ቤት ከወሰነላቸው ሦስት ጓደኞሞች መካከል አንደኛው ብር አጥቶ ሳይፈታ ይሰነብታል። የእርሱ የቅርብ ዘመድ የሆነ ችግሩ መፈጠሩን ሰምቶ ከመተማ አካባቢ መጣ። ስለመኖር አለመኖሩ እርግጠኛ አይደለም። ሆስፒታል አስከሬን ክፍል ከተደረደሩ አስከሬኖች መካከል ፈልግ መባሉን ሆኖም እንዳጠው ገልጧል። ረቡእ ጠዋት አንገረብ አጠገብ ወደተሰራው አዲስ ማረሚያ ቤት ታሳሪዎች ተዛውረው ነበር።

ሐሙስ ጠዋት የታሰረ ዘመድ ያላቸው ሰዎች ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ ወደ አዲሱ ማረሚያ ቤት ምግብ ይዘው ወረዱ። ዋና ዓላማቸው ግን ምግብ መውሰድ አልነበረም፤ በሕዳር 21 ቀኑ ጭፍጨፋ መትረፍ አለመትረፋቸውን ለማረጋገጥ ነው እንጅ። ልዩ ኃይል ፖሊሶች መቅረብ አትችሉም ሲሉ ከለከሉ። ከውስጥ የሕግ ታራሚዎች ‹‹በረኀብ አለቅን›› የሚል ድምጽ ከብዙ ርቀት ይሰማ ነበር። በግምት ከረፋዱ 5፡00 ይሆን ነበር። እስከ አፍንጫቸው የታጠቁ የፖሊስ አባላት በፒያሳ መስቀል አደባባይ አድርገው ወደ አዲሱ ማረሚያ ቤት ገሰገሱ። ሕዝቡን ለማስፈራራት ይመስላል። ከውጭ በጠያቂና በፖሊስ ከውስጥ በታራሚና በፖሊስ መካከል ግጭት ተከሰተ። ግቢ ውስጥ ያለው እሳር ተቃጠለ። ከውጭ በኩል የሄደው ጠያቂ መትረጊስ ሲጮኽበት በድንጋይ መመለስ እንደማይችል በመገንዘብ ተበተነ። ውስጥ ያሉት ግን ከመረሸን አላመለጡም። እነሆ ሐሙስ ሕዳር 23 ቀን የተጨማሪ ሰዎች ደም ፈሰሰ። የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ሙታንንና ቁስለኞችን ተቀበለ። እንደተለመደው ሆስፒታሉ ተዘጋ። አንድ የልዩ ኃይል ፖሊሲ በዚህ ቀን የሞቱት 7 ናቸው ብሎኝ ነበር። ሆኖም ከሆስፒታል ባገኘሁት መረጃ ግን የሟቾች ቁጥር 21 ነው። ከነዚህ ውስጥ 2ቱ ከገቡ በኋላ ነው ሕይወታቸው ያለፈው።

ሐሙስ ለአርብ ሌሊት ከእንቅልፌ የቀሰቀሰኝ የሰዎች መሪር ለቅሶ ነበር። ቀኑን የተገደሉ ሰዎች አስከሬን ለቤተሰቦቻቸው ከተሰጠ በኋላ በመለዋ ጎንደር ለቅሶና ዋይታ ሆነ። ቀበሌ 18 ከአንደኛው ሟች ቤት ሄድኩ። ሐዘን ቤት ብዙ ቦታ ሂጄ አውቃለሁ። ለምን እንደው ባላውቅም ግን ከዚህ ቤት የነበረው ሐዘንና የቤተሰቦቹ ሐዘን ከእስካሁኑ የተለየ አደረገብኝ። ቲኬት አልነበረኝም፤ ግን ጎንደር በመቆየት ሐዘኑን መቋቋም አቅም አጣው። ለሁልጊዜው የማልሰለቻት ጎንደርን አርብ ጠዋት ትቻት ወጣሁ።

(ይህ ጽሑፍ የተዘጋጀው ቦታው ድረስ በመሄድ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከጎንደር ከተማ ነዋዎችና ከተጎጅ ቤተሰቦች እንዲሁም ከጥቂት የፖሊስ መኮነኖች በተለያየ መልኩ በማጣራት ነው።)



# “በብሔረሰቦች መካከል...

በሌላ በኩል ፍርድ ቤት ከለቀቃቸው በኋላ ደግሞ ሰዎቹን ወህኒ ቤት ማቆየት ከፍተኛ ሕገ ወጥነት ነው፡፡ የመንግሥት አካል ሦስት ነው - ሕግ አውጭ፣ ሕግ ተርጓሚና ሕግ አስፈጻሚ፡፡ እነኚህ ሦስቱ ለየብቻ እንዲሠሩ ነው የሚጠበቀው፡፡ በዳኞቹ ውሳኔ ሕግ አስፈጻሚው ጣልቃ ሊገባ አይገባም፡፡ የዳኛ ውሳኔ ካልተፈጸመ በአገሪቱ ውስጥ መንግሥት አለ ማለት አይቻልም፡፡ ዳኞቹ በነጻነት ሥራቸውን እስካላከናወኑ ድረስ የመንግሥት መዋቅር አለ ማለትም አይቻልም፡፡ አንድ ሰው በተከሰሰበት ወንጀል ፍርድ ቤት በነጻ ሲለቀው ይህ የመጨረሻ ውሳኔ ነው፡፡ ሕግ አስፈጻሚው የሚያገባው ነገር የለም፡፡ ፍርዱ ትክክል አይደለም ካሉ ይግባኝ ሊሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ሕግ አስፈጻሚው የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ ሽሮ አትፈታም ይላል፡፡

**የብሔር ብሔረሰቦች በዓል በሚከበርበት ወቅት ተደጋግሞ የሚነገር ነገር አለ፤ ኢትዮጵያ የብሔረሰብ ፌደራሊዝምን መከተል ከጀመረች ወዲህ ብሔራዊ መግባባት መጥቷል፤ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ተፈጥሯል ወዘተ. ይባላል። ይሁን እንጂ ደግሞ በየአካባቢው ብዙ ዜጎች ይፈናቀላሉ፤ በሕዝቡ መካከልም ጥርጣሬና አለመተማመን አለ። በአገዛዙ በኩል የሚነገረውና ተጨባጩ እውነታ እንዴት ነው የሚታረቁት?**

እንደኔ ዕይታ አገራችን ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ነው ያለችው፡፡ በየብሔረሰቡ ያለው አለመተማመን፣ መናቆርና ጥላቻ ወደ መጥፎ ነገር ሊያመሩ ይችላል፡፡ ከዚህ በፊትም በተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ ያቅሜን ያህል ለማሳሰብ ሞክሬያለሁ፡፡ ቀደም ሲል ካለኝ ተመክሮ ተነስቼ ሳየው አሁን ያለው ሁኔታ በጣም በጣም ይረብሸኛል፡፡ እንዳልኩት በጋዜጣም አንዳንድ ነገሮችን ለማመልከት ሞክሬያለሁ፤ በግልም ደረጃ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ለመነጋገር ሞክሬያለሁ፡፡ ቅን የሆነ ውይይትና ምክክር ተደርጎ ብሔራዊ እርቅ የሚወርድበትን ምክንያት እንፈልግ ተባብለን ተነጋግረን ነበር፡፡ የትም ግን አልደረሰም፡፡ ካሁኑ ብንነቃ ይሻላል፡፡ በየቦታው በጣም መጥፎ ሁኔታ ነው ያለው፡፡ የምንሰማው የብሔረሰብ ግጭት ነው፤ አንዱ አንዱን በጥላቻ ነው የሚያየው፡፡ ይኸው በኦሮሚያና በጎንደር ስንት ሰው ነው የሚታሰረው የሚገደለው፡፡ ሰላም አለ ማለት አይቻልም፤ ሰላም የለም፡፡ በየአካባቢው ሰዎች ይታሰራሉ፤ ይገደላሉ፡፡ ብሔረሰቦች ይጋጫሉ፡፡ ስለዚህ በጊዜ ካልነቃን ወደ መጥፎ ሁኔታ ሊያመራ ይችላል፡፡

እኔ በአንዳንድ በሠራሁባቸው አገሮች ያየሁት ነገር በአገሬ እንዲከሰት አልፈልግም፡፡ የማይሆን ስም ሊያሰጠኝ የሚችል ቢሆንም ጉዳዩ የአገርና የሕዝብ ጉዳይ ነውና አበክሬ ማሳሰብ እፈልጋለሁ፡፡ አገራችን መጥፎ መንገድ ላይ ነው ያለችው፡፡ በተለይ በብሔረሰቦች መካከል ያለው ግንኙነትና ጥላቻ በጣም የሚረብሽ ነው፡፡ ወደ መጥፎ ሁኔታ ሊያመራ ይችላል፡፡ ከዚህ በፊት በሠራሁባቸው አገሮች እንደኔው አንዳንድ ሰዎች አስቀድመው አስጠንቅቀው ነበር፡፡ ሲያስጠነቅቁ ‹‹አይ እነዚህ ሟርተኞቸ ናቸው›› ተብለው ሌላ ሌላም ስም ተሰጥቷቸው ተፈረጁ፡፡ ሆኖም ግን ወደኋላ ጉዳቱ መድረሱ አልቀረም፡፡ በእኛም አገር ቢሆን ሲዘራና ሲኮተኮት የከረመው የልዩነትና የጥላቻ ፖለቲካ ያፈራውን ፍሬና መሬት ላይ ያለውን ተጨባጩን ሁኔታ ሳያጤኑ አንዳንድ ወገኖች ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ ግንኙነት ጥልቅ ነው›› ወዘተ. ሲሉ ይሰማል፡፡ በበኩሌ እንደዚህ ያለው አስተያየት ውኃ የሚቋጥር አስተያየት አይመስለኝም፡፡ አዎ፣ ግኙነታችን በጣም ጥልቅ ነው፤ ግን ደግሞ ባለፉት ዓመታት ሲዘሩ የከረሙት አደገኛ ነገሮች ፍሬ ማፍራት ጀምረዋል፤ ለዚህም ነው በየአካባቢው ኢትዮጵያውያን በአገራቸው እንደስደተኛ እንዲያውም ከዚያ ባነሰ ሁኔታ ተቆጥረው የሚባረሩትና የሚፈናቀሉት፡፡ ቶሎ ብንነቃ ይሻላል፡፡ ያለው ሁኔታ በፍጹም ደስ የሚል አይደለም፡፡ ሰሞኑን ጎንደር ውስጥ የሆነውን እናያለን፡፡ በኦሮሚያ አካባቢ የሚሆነውን እያየን ነው፡፡ የአገሪቱ ሰላም አንዴ ከደፈረሰ መልሶ ሰላምን ማምጣት በጣም አደገኛ ነው የሚሆነው፡፡ ነገሮች ወደ መጥፎ ሁነታ ሳየሄዱና ሳይካረሩ ብሔራዊ እርቅ መምጣት አለበት፡፡ ብሔራዊ እርቅ ሲባል እንዲያው ተጨባብጦ ‹‹እንደምን ነህ፤ ደህና ነህ ወይ›› መባባል ሳይሆን የመናገርና የሐሳብ ነጻነቶች ተለቀው ሥርዓት ባለውና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መነጋገር አለብን፡፡ ኮንፈረንሶችና የውይይት መድረኮችም ያስፈልጋሉ፡፡ አማራጩ ወይ ዴሞክራሲን ማምጣት አለዚያም መጥፋት ነው፡፡ ማንም ደግሞ መጥፋትን አይመርጥም፡፡ በሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር መንግሥት አንደኛ በአስቸኳይ የፖለቲካ እስረኞችንና የሃይማኖት መሪዎች በሙሉ መፍታት አለበት፡፡ ሁለተኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለፍርሐት እንዲንቀሳቀሱ የጸረ ሽብር አዋጁና ሌሎችም የሰውን መብት የሚገድቡ ህጎች መሰረዝ አለባቸው፡፡

በአገራችን የሕዝብ መግባባት፣ ብሔራዊ መግባባት በጣም ያስፈልጋል፡፡ ሕዝቡ በብሔረሰብ ተከፋፍሏል፡፡ በጣም መጥፎ አቅጣጫ እየታየ ነው፡፡ በየጊዜው እየባሰ ነው እየሔደ ያለው፡፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሊያሳስበው የሚገባ ነገር ነው፡፡ ብሔራዊ እርቅ ያስፈልጋል፡፡ ብሔራዊ እርቅ ስንል ቅድም እንዳልኩት ተሳስሞ መለያየት አይደለም፡፡ የሕዝቡን መብት እያከበሩ በውይይት ችግሮችን መፍታት ነው፡፡ ይኼ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሁሉ ማጠቃለል አለበት፡፡ አሁን ከኢሕአዴግ ጋር የሚሠሩ ተቃዋሚ ተብየ ፓርቲዎች አሉ፡፡ እነርሱ በእውነት ለአገሪቱ መፍትሔ የሚሰጡ አይደሉም፡፡ እንዲያውም በኔ እምነት ሽብርተኛ ተብለው ከተፈረጁ ፓርቲዎችም ጋር ቢሆን ውይይት መደረግ መቻል አለበት፡፡ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ሊያሳስብ የሚገባ ነገር ቢሆንም በተለይ አሁን በመሪነት ላይ ያሉ ሰዎች ኃላፊነት አለባቸው፡፡ እንዲያውም ተጠያቂነት አለባቸው፡፡

በጎንደርም በኦሮሚያ አካባቢም የተከሰቱት ነገሮች ከሕዝብ ጋር ሰላማዊ ውይይት በማድረግ ሊፈቱ ይችላሉ፡፡ በመሠረቱ ሕዝብ ሰላማዊ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ረብሻን፣ ንብረቱ እንዲወድሙበትና እንዲቃጠልበት፣ ልጆቹ እንዲሞቱበት አይፈልግም፡፡ ያላቸውን ጥያቄ ሰሚ ኖሮ በውይይት ከተሰሙ ማናቸውንም ጥያቄ ይፈታል፡፡ አሁን ያለው አንድ ፓርቲ ነው፡፡ ያ ፓርቲ ከማንም ጋር ውይይት አያደርግም፡፡ ተቃዋሚዎች ጋር ውይይትም መግባባትም የለም፡፡ በሕዝቡ በኩልም ምንም የሚንቀሳቀስ ነገር የለም፡፡ ከሕዝብ ጋር ተገናኝቶ መነጋገርና መግባባት የለም፡፡ በአገራች ውስጥ የተከሰቱ ነገሮች ሁሉ በውይይት ሊፈቱ የሚችሉ ናቸው፡፡ አማራጩም ይኸው ብቻ ነው፡፡ በውይይት ካልፈታናቸው ወደ ሌላ አቅጣጫ ሊያመሩ ይችላሉ፡፡ በአንዳንድ ወገኖች ይህ አባባል ላይወደድ ይችላል፡፡ ነገር ግን የአገር ጉዳይ ስለሆነ መነጋገር ያስፈልጋል፡፡

በአስተያየቱ ብሳሳት ምንኛ ደስ ባለኝ፡፡ ሆኖም በሥራ ዓለም ሆኜ ያየዋቸው አሰቃቂና ለጠላት እንኳን የማይመኙት ሁኔታዎች ችግሩን አግዝፌ እንዳይ አድርጎኝ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ እንዲሉ የገለጽኳቸው የሰላም ሒደቶች ይጠቅማሉ እንጅ አይጎዱም፡፡ ምነው በአገራችን የተከበሩ ሽማግሌዎች እነ ልዑል ራስ ስዩም፣ እነ ፕ/ር መስፍን፣ እነ አቶ ሽመልስ አዱኛ ዝምታ አበዙ፡፡ እንደ አገር አባትነታቸው በዚህ ጉዳይ ላይ እጃቸውን የመስደድ ግዴታና መብትም አለባቸው፡፡

# “ዘመን የመጣለት” ...

ይዞት የነበረውን ፖለቲካዊ ከባቢ በትቂቱም ቢሆን ዘና ለማድረግ ሞክረዋል፡፡ የፖለቲካ እስረኞችን መፍታታቸውና የፕሬስ ነጻነቱን አሽመድምዶ የነበረውን የቅድመ ምርመራ አሠራር ማንሳታቸው የመጀመሪያው እርምጃቸው ነው፡፡ ዘንድሮ የተደረገው ምርጫ ተቃዋሚዎችን ያሳተፈ ብቻ ሳይሆን ላሸናፊው ፓርቲ ሥልጣን እስከመልቀቅ የደረሰ ዝግጁነት እንዲያሳይ ያደረገ መለወጥ በወታደሮቹ ዘንድ ታይቷል፡፡ በመሆኑም በበርማ ሕዝብ ዘንድ እጅግ የሚጠላው ወታደራዊ መንግሥት የሳንሱቺ ፓርቲ መንግሥት ለመመሥረት የሚያስችለውን የፓርላማ ወንበር እንዳገኘ አምኖ ስልጣን ለማስረከብ እየተንደረደረ ነው፡፡

በገታራ አምባገነናዊ አቋም ከሚታወቀው የአገራችን መንግሥት ጋር የመንትያ ያህል ምስስሎሽ የነበረው የበርማ መንግሥት በምን ምክንያት ሦስት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ለውጥ አመጣ የሚለው ትልቅ ጥያቄ ነው፡፡ ለለውጡ ዓይነተኛ ምክንያት ተብሎ የሚጠቀሰው በአገሪቱ መንግሥት የቀድሞ አንባገነናዊ አቋም ምክንያት ከምዕራባዊያን የወረደባት ከባድ ማዕቀብ ኢኮኖሚዋን ማሽመድመዱ ነው፡፡ የበረሩ ነጋዴዎች እንደሆኑ የሚነገርላቸው የበርማ ወታደራዊ ባለሥልጣናት ታዲያ በዚህ ማዕቀብ ባልፈሰፈሰው ኢኮኖሚ ንግዳቸውን ማጧጧፍ ስለተሳናቸው አረማመዳቸውን ከምዕራባዊያን ጋር ማስተካከል ነበረባቸውና ለውጡን አመጡ፡፡ ይህ በብዙ ተንታኞች ዘንድ ተቀባይነት ያለው ትንታኔ ነው፡፡ እዚህ ላይ የማይታለፈው ጥያቄ ምዕራባዊያኑ በበርማ ላይ ያደረጉትን የማዕቀብ መጣል ቁርጠኝነት በመንትያዋ ኢትዮጵያ ላይ ለማሳየት ለምን ተሳናቸው የሚለው ነው፡፡ ለዚህ መልሱ የአገራችን መልካምድራዊ አቀማመጥ እና የወታደራዊ ጉልበቷን የትም ለመላክ ያላት አቤት ወዴት ባይነት በምዕራባዊያኑ ዘንድ የምሥራቅ አፍሪካ የሰላም አለቃ ተደርጋ እንድትቆጠር ረድቷል፡፡ እግረ መንገዱንም ሕዝቦቿ የዴሞክራሲ ጸሐይ እንድትዘገይባቸው ምክንያት ሆኗል፡፡

## ያላለቀው ፈተና


ለዴሞክራሲ ምጽዓት ዝንባሌ አሳይተዋል የተባሉት ወታደሮች የለውጣቸው ምክንያት በምዕራባዊያኑ የተጣለባቸው ማዕቀብ የራሳቸውን ቢዝነስ ለማሳደግ እንቅፋት ስለሆነባቸው ነው የሚለው ትንታኔ ሚዛን የሚደፋው አሁንም በርማ ላይ የተደቀነው ፈተና ስናጤን ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ወታደሮቹ ለለውጥ ዘንበል አሉ የተባለው በ2011 በተደረጉት ለውጦች ምክንያት ነው፡፡ ሆኖም ይህ ለውጥ የምዕራባዊያኑን ማዕቀብ ከማስነሳት በዘለለ ልባዊ የዴሞክራሲ ናፍቆት ያመጣው እንዳልሆነ የሚያሳዩ ብዙ ምልክቶች ናቸው፡፡ እ.ኤ.አ. በ2008 ዝገ ሸዊ የተባሉ ወታደራዊ አምባገነን አገሪቱን በሚመሩበት ወቅት ሕገ መንግሥቱን ለማሻሻል ሪፈረንደም ተካሂዶ ነበር፡፡ይህ ሪፈረንደም ወታደሩ የአምባገነንነቱን ዘመን የማስረዘሙን መሰሪ አካሄድ በሕገ መንግሥት አንቀጽ አትሞ ያስቀመጠበት ነው፡፡

በዚህ ሪፈረንደም ወታደሩ የፓርላማ መቀመጫውን ሃያ አምስት በመቶ ወንበር በቀጥታ በሚሰይማቸው ባለሟሎቹ እንዲሞላ ሥልጣን የሚሰጥ ሕገ መንግሥታዊ አንቀጽ ተደንግጓል፡፡ ይህም አይበቃም ሕገ መንግሥቱን ስለማሻሻል በሚያወራው አንቀጽ ላይ ደግሞ በአገሪቱ ሕገ መንግሥታዊ አንቀጽን ለማሻሻል ከሰባ አምስት በመቶ በላይ ድምጽ ማግኘት ግድ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ በሌላ አባባል ሕገ መንግሥቱን ለማሻሻል የወታደሩ ይሁንታ ግድ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ወታደራዊ መንግሥቱ ሕገ መንግሥታዊ ለውጥን በተመለከተ ድምጽን በድምጽ የመሻር ሥልጣን ተከናንቧል፡፡ ይህ በሪፈረንደም ተደረገ የተባለው ሕገ መንግሥታዊ መሻሻል የውጭ ዜጋ ያገባ/ች እና የውጭ ዜጋ ልጆች ያለው/ያላት የበርማ ዜጋ የአገሪቱ ፕሬዚደንት መሆን አይቻለውም ሲል ይከለክላል፡፡ ይህ አንቀጽ ሟች እንግሊዛዊ ባል የነበራቸውንና ሁለት ልጆቻቸውን እንግሊዝ አገር የወለዱት ሳንሱቺ በርማን ፕሬዚደንት ሆነው እንዳይመሯት ይከለክላል፡፡ እንደውም ሕጉ የወጣው ሳንሱቺ እየታሰቡ ይመስለላል (ይሄ ነገር በሚገርም ሁኔታ እኛ አገር አቶ ስየ እየታሰቡ የተረቀቀ የሚመስለውን፣ በአንድ ጀንበር ተግባራዊ የሆነ የጸረ-ሙስና ሕግ ያስታውሳል፡፡)

እንዲህ በሕገ መንግሥታዊ አንቀጽ የተደገፈው ፖለቲካዊ አሻጥር በቅርብ የሚፈታ የማይመስለው የበርማ ውስብስብ ፖለቲካዊ ሕማማት ሥር ነው፡፡ ምክንያቱም በርማ ተያያዘችው የተባለውን ዴሞክራሲያዊ ጉዞ ሕላዊ ለማድረግ ወታደሩ ከፖለቲካውና ከኢኮኖሚው ገለል ማለት አለበት፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ሕገ መንግሥቱ ተሻሽሎ አገሪቱ የሲቪል መንግሥትን የምታቋምበትን ሕጋዊ መሠረት ማበጀት አለባት፡፡ ሕገ መንግሥቱን የማሻሻሉን ነገር በወታደሩ አፈሙዝ ዙሪያ ተብትቦ ያስቀመጠው አሁን የሚሠራው ሕገ መንግሥት ግን ለሁሉም የወታደሩን ቡራኬ ይጠይቃል፡፡ ወታደሩ ደግሞ ይህን በጀ እንደማይል ከዓመት በፊት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ፊርማ አሰባስበው ሕገ መንግሥታዊ ለውጥ ሲጠይቁት ፈርጠም ብሎ ‹‹ይህ አይሆንም›› ሲል እንቅጩን ተናግሯል፡፡

ሌላው ፈተና ከሳንሱቺ ፓርቲ ተተኪ ያለማፍራት ችግር የሚመነጭ ይሆናል፡፡ የበርማ ፖለቲካ ከአገራችን ፖለቲካ ጋር የሚመሳሰለው በገዥዎች አንጻር ብቻ አይደለም፤ ከተቃዋሚዎችም ጭምር እንጅ፡፡ ልክ እንደአገራችን በበርማም ከፓርቲ ፕሮግራምና የርዕዮት ዓለም መስመር ይልቅ የመሪዎች ስብዕና ይገዝፋል፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሁልጊዜ በተመሳሳይ መሪዎች ከመመራታቸው የተነሳ የሚጠሩት በፓርቲው ሳይሆን በመሪዎች ስም ነው፡፡ ዕድል ቀንቶ ሥልጣን ቢያዝ ይህ ፈለግ ወደ አምባገነንነት የማያድግበት መንገድ አይታየኝም፡፡ እንደዚህ ዓይነት ፓርቲዎች እንታገለዋለን ከሚሉት አምባገነን መንግሥት የሚለያቸው ምናልባት ሥልጣን እንደሰማይ ስለራቃቸው ብቻ ይሆናል፡፡ የሆነ ሆኖ ከላይ የተጠቀሰው ሳንሱቺን ፕሬዚዳንት እንዳይሆኑ የሚከለክለው አንቀጽ ተተኪ ላላፈራው የሳንሱቺ ፓርቲ ትልቅ ፈተና ደቅኗል፡፡ ስለዚህ ሲጠየቁ ሳን ሱቺ ‹‹በግልጽ አንድ ሰው ፕሬዚደንት አድርገን እኔ ከላይ እመራዋለሁ›› ሲሉ የእጅ አዙር አምባገነንነትን ጅማሬ እንደ ጥሩ መፍትሔ ተናግረዋል፡፡ በመረጡኝ ዘመቻቸው ላይ ጭምር ፓርቲያቸው ወደፊት ሥልጣን ሲይዝ የአገሪቱን ፖለቲካዊ ሕማማት በማስወገዱ በኩል ያለውን ፖሊሲና እስትራቴጂ በተመለከተም ወይዘሮዋ ፖለቲከኛ እዚህ ግባ የሚባል ነገር አልተናገሩም፡፡ በምርጫ ቅስቀሳው ወቅት ከቤቱ በነቂስ ወጥቶ የሚከተላቸው አጀባቸውም የሚያጨበጭብላቸው አንድም ወታደራዊውን መንግሥት ከመጥላት አለያም የእርሳቸውን ግላዊ ፖለቲካዊ ማንነት የዓላማ ጽናት በማድነቅ ይመስላል፡፡

የሳንሱቺ ፓርቲ መንግሥት ሊያስመሠርት የሚችልበትን ድምጽ አግኝቷል ቢባልም ያሸነፈው ወታደራዊ ደጀን ያለውን የወታደራዊው መንግሥት የሲቪል ክንፍ ከሆነውን ‹‹Union Solidarity and Development Party›› (USDP) እንጂ በአገሪቱ በሰፊው የተዘረጋውን የወታደራዊውን መንግሥት ክንድ አይደለም፡፡ የሳንሱቺ ፓርቲ የፕሬዚደንትነቱን ቦታ ቢይዝም የአድራጊ ፈጣሪነቱን ሚና የሚይዘው ወታደራዊ ክንፍ አሁንም ከነረቨምና ጠንካራ እጁ በሕገ መንግሥታዊ አንቀጽ ተደግፎ ይኖራል፡፡ ሕገ መንግሥቱን የማሻሻሉን ጉዳይ ቀይ መስመር ውስጥ ያለ ጉዳይ አድርገው ካስቀመጡ፣ ይህ ሲነሳባቸው ቶሎ ደማቸው ከሚፈላ ወታደሮች ጋር ተነጋግሮ ለውጥ ማምጣቱ ለሳንሱቺ NLD ፓርቲም ሆነ ለራሳቸው ትልቅ ፈተና ነው፡፡ ወታደራዊው መንግሥት እስካሁን ባደረጋቸው የላይ የላይ በጎ እርምጃዎች ብቻ በመርካት በሕገ መንግሥታዊ አንቀጽ የተተበተበውን የአምባገነንነት ደጀን እንዲያነሱ ሳይጠበቅ ምዕራባዊያኑ በአገሪቱ ላይ ጥለውት የነበረውን ማዕቀብ በፍጥነት አንስተዋል፡፡ ይህ ነጋዴ ወታደራዊ ባለሥልጣናቱ የፈለጉትን እንዲያገኙ አድርጓል፡፡ የፈለጉትን ኢኮኖሚያዊ መነቃቃት ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት በሚመጣው የገንዘብ ፍሰት ያስተማመኑት ጄነራሎች ታዲያ ሕገ መንግሥታዊ ለውጡን ያፋጥኑታል ተብሎ እንደማይታሰብ ተንታኞች እየገለጹ ነው፡፡ ይህ ለወታደሮቹ መልካም ሲሆን ለሳንሱቺ ግን ትልቅ ራስ ምታት ነው፡፡ የተፋፋመውን የብሔር ፖለቲካ በማስከኑ ረገድም ወይዘሮዋ ቀላል የማይባል ተግዳሮት አለባቸው፡፡



## ታሪክና ኅብረተሰብ

ታዬዎስ ታንቱ
(የስልክ ቁጥር:- 0934996138 ፣ የመ.ሳ. ቁጥር:- 43414)

# የግፍ አገዛዝን ከነግሳንግሡ ለማስወገድ

አንዳችም ተጠየቃዊ ምክንያት በተጨማሪ ሳናመጣ በአንድ አገር ህዳጣን ብዙኃንን ከገዙ የግፍ አገዛዝ እንደተንሰራፋ በእርግጠኛነት መናገር ይቻላል:: ክርክር አያስፈልገውም:: ሙግት አያሻም:: ብዙኃን ህዳጣንን ተሸክመው የሚኖሩበት አቻ የማይገኝለት የግፍ አገዛዝ ነው:: ሥልጣነ ሕዝባዊ የሥነ መንግሥት አሰራርን በግልጽ ይጻረራልና:: በዚህ መነሻ በዛሬው ዓለም ህዳጣን ብዙኃንን ሊገዙ ቀርቶ ብዙኃን ራሳቸው እንኳን በአስተዳደሩ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሒደት የህዳጣንን የሥነ መንግሥት አቋም ከግምት ማስገባት ይጠበቅባቸዋል:: ዓለም ሰልጥኗል:: በዘፈቀደ ሰው ሰውን የሚገዛበት አካሄድ ቦታ አጥቷል:: የኢትዮጵያ ሁኔታ የሕዝቡን ድክመት ያሳያል:: ደካማ ሕዝብ በግፍ አገዛዝ ይማቅቃል:: ፈሪ ሕዝብ በባርነት ይኖራል:: ስለእውነት በእውነት ልንነጋገር ይገባል:: ፈሪ ሕዝብ በነጻነትና በባርነት መካከል ያለውን ልዩነት እንኳን አይረዳም:: ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብም በነጻነትና በባርነት መካከል ያለውን ልዩነት እንደማይገነዘብ ይስተዋላል:: ለዚህ ነቃሽ ፍለጋ አንሄድም:: ከቀያቸው ችጋር ያባረራቸው መጤዎች እንደፈረስ ለጉመው ሲጋልቡት በይሁንታ መቀበል በራሱ በቂ ምስክር ነው:: በዚህ ድክመታችን ለሃያ አምስት ቀናት በሥልጣን ላይ መቆዬት እንኳን የሌለባቸው ምልምል ባንዳዎች ለሃያ አምስት ዓመታት ሊገዙን በቅተዋል::

የዓለም ሕዝብ በስልጣኔ ሒደት ላይ ይስተዋላል:: ጉዞ ወደፊት ሆኗል:: ታዲያ ወደኋላ የቀረንበት ምክንያት ምንድን ነው? ከተቀረው የዓለም ሕዝብ በምን እናንሳለን? ተጨባጭና አሳማኝ ምክንያት የለንም:: ከግላችን የሰረጸ ድክመት ሕይወታችን ሊወስን በቅቷል:: የግፍ አገዛዝ ሰለባ ሆነናል:: ልናፍር ይገባል:: አሁንም ግን አቋማችን ልናስተካክል እንደምንችል አንርሳ:: ወንበዴ አገር አይገዛም:: ወንበዴ ሕዝብ አያስተዳድርም:: ወንበዴ ተግባሩ ምን እንደሆነ እሱ ራሱ ያውቃል:: አሳምሮ ያውቃል:: ወንበዴ ተግባሩ የንጹሓንን ደም በግፍ ማፍሰስ ነው:: ወንበዴ ተግባሩ የዜጎችን ንብረትና ገንዘብ መዝረፍ ነው:: ይህ የወንበዴ ሥራ ነው:: ወንበዴን በሥሙ እንጥራው:: ቆንጆ ሥም አለው:: ተግባሩን የሚወክል ሥም አለው:: ማሰብ በህግ የተከለከለን ይመስላል:: ማሰብን የሚከለክል ሕግ ግን የለም:: የተፈጥሮ ህግ የማንነታችን አካል ነው:: ማሰብን ያበረታታል:: ማስተዋል ከማሰብ ይመጣል:: ማመዛዘን ከማስታዋል ይፈልቃል:: ለምን እንደማናስብ ግን አይገባንም:: በዝግመተ ለውጥ ከሰውነት ደረጃ እየተቀየርን ይሆን እንዴ? በፍጹም! በሥነ ሕይወታዊ አካላችን ከአፍሪቃም ሆነ ከተቀረው የዓለም ሕዝብ የተለየን አየደለንም:: ሰዎች ነበርን:: ሰዎች ነን:: ይህ ከሆነ ደግሞ በሥልጣኔ የተራመድነው የዓለም ሕዝብ ያደረገውን ሁሉ ልናደርግ ይገባል::

ዛሬ ግፈኞች ጨምድደው ይዘውናል:: በእግረ ሙቅ ታስረናል:: በሰንሰለት ተቆራኝተናል:: ለእያንዳንዱ ዜጋ በሕይወት ለመኖር እንኳን የአንድ ተራ የአገዛዙ ታጣቂ መልካም ፈቃድ አስፈልጓል:: ግፉ አሻቅቧል:: ሞት ነግሷል:: የወህኒ ቤት ልማት በልማታዊ ከበርቴዎች ተሳትፎ ተጠናክሮ ቀጥሏል:: ቅልብ ነፍሰ ገዳዮች በገፍ ሰልጥነዋል:: ኢትዮጵያ አገራችን ያለ ጥርጥር የሰፊው ሕዝብ እስር ቤት ናት:: በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሥነ መንግሥት ሥልጣን በያዘ አካል እንዲህ ያለ ግፍ የተሰራበት ዘመን ፈጽሞ አልነበረም:: ሰው ክቡር ነው:: ወንበዴዎች እንኳን ራሳቸውን እንደሰው ሲቆጥሩ ይስተዋላል:: ንጹሑን ሰው ግን ሳያቅማሙ በጥይት ተኩሰው ሲገድ ይታያል:: ሰውን ዋጋ የሌለው ፍጡር አድርገዋል:: ለሰው ልጅ ክብር ነፍገዋል:: በግፍ ይገዙናል:: በግልጽ ይዘው ያስሩናል:: በሚስጥር ይገድሉናል:: የአንድ መንደር ምልምሎች ጊዜ ሰጥቷቸዋል:: ከብረዋል:: ሕዝብን አደህይተው በልጽገዋል:: በዘር ሥሌት ዙፋን ይዘዋል:: ድህነታቸውን ታሪክ አድርገዋል:: ይሉኝታ ከማያውቅ ዘር መፈጠራቸው የጥፋት ሥነ ልቦናቸውን አሳድጎላቸዋል:: ትናንት መጥረጊያና መወልወያ ተሸክመው በየሰፈሩ እየጮኹ ይዞሩ እንደነበር ረስተዋል:: በቆልቲ መሸጥ ትተዋል:: የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ:: የቀድሞ ሥራቸውን ሌላ ሰው እንኳ እንዳይሰራ ባቄላ ከአገር እንዲጠፋ አድርገዋል:: የንጉሥ ምቀኛ ሆነዋል::

ገዢዎቻችን ግፈኞች ናቸው:: እነርሱ የኢትዮጵያን የሥ መንግሥት የሥልጣን እርካብ ከረገጡበት ወቅት አንስቶ መልካም ነገር አላየንም:: አንዳችም መልካም ነገር በዚህች አገር በእነርሱ የአገዛዝ ሂደት አልተስተዋለም:: ድህነት አሻቅቧል:: የዋጋ ንረት ወደሰማየ ሰማያት ተንጠራርቷል:: የዜግነት መብታችን ተገፏል:: ሁሉም ከኢትዮጵያዊነት አፈንግጦ በየጎሳው እንዲባደን ታውጇል:: ውለን ለመግባት እንኳን ዋስትና አጥተናል:: ሞት ረክሷል:: ሕይወት በተስፋ ያልፋል:: የግፍ አገዛዝ እንክርዳድ አፍርቷል:: ገዢዎቻችን በጥፋት ተግባራቸው አሁንም ቀጥለዋል::

ሥርዓተ አገዛዙ ከእኩይ ድርጊቱ ከቶም አይታረምም:: አንዱን ጎሳ ከሌላው ጋር በማጋጨት ተግባሩ ዛሬም አልታቀበም:: ገዢዎቻችን በእብሪት ተወጥረዋል:: ልባቸው ደንድኗል:: ዛሬም ዜጎች ወልደውና ከብረው ከኖሩበት መንደር ሲፈናቀሉ ይስተዋላል:: በዘራው ምክንያት በጥይት ተደብድበው ተገድለዋል:: በየጎሳው ነፍሰ ገዳይ ታጣቂዎችን በሚስጥር ሰግስገዋል:: የግፍ አገዛዝ እየከፋ ሂዷል:: ቃላት ሊገልጹት ከሚችሉት እንኳን አሻቅቧል:: ያም ሆነ ይህ አገራችን ለግፈኞች ለቀን የትም ላለመሄድ አቋም ወስደናል:: ኢትዮጵያን የጋራችን ለማድረግ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ሆነን መታገል እንዳለብን ጽኑ አቋም ይዘናል:: የግፍ አገዛዝን ከእነ ግሳንግሱ ወደ ታሪክ ትቢያነት ለመቀየር ትግል ያስፈልጋል:: ትግል የግድ ይላል:: ‹‹ውርደት ይብቃን›› ማለት ይኖርብናል:: ግፍ በምን ይለካል? ለአያሌ ጊዜ ተነጋግረናል:: ሕዳጣን ብዙኃን ከገዙ በአንድ አገር ላይ ግፍ ነግሷል:: ለሃያ አምስት አመታት በግፍ ማቅቀናል:: የመከራ ቀንበር ተሸክመን ኖረናል:: በግፍ ተገዝተናል:: ለስንት አመታት በባርነት እንቀጥል?

ገዥዎቻችን የግፍ አገዛዝ እድሜያቸውን ለማራዘም በተለይ ከልዩ ልዩ ጎሳዎች የመለመሏቸውን ሎሌዎቻቸውን ለመሣሪያነት በከፍተኛ ደረጃ ተጠቅመዋል:: እየተጠቀሙም ነው:: እነዚህ ለባንዳ ጌቶቻቸው በሎሌነት ያደሩ የጎሳ አምበሎች ላለፉት ሃያ አምስት አመታት በተለይ አንዱን ጎሳ ከአጎራባች ወገኑ ጋር ለማጋጨት የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሌት ተቀን ሰርተዋል:: በትጋት ፈጽመዋል::

ለሎሌነታቸው የሚመጥን ሹመትና ሽልማትም አግኝተዋል:: እነዚህ የበሉበትን ወጭት ሰባሪዎች ኢትዮጵያን እናታቸውን ለሚያዋርድ ተግባር ሁሉ ንቁ ሆነው ቆመዋል:: የገዥዎቻችንን ፍላጎት ተከትለው ሕዝብን ከሕዝብ ለማጋጨት ልዩነቶችን አጉልተው በዜጎች መካከል አንድነት መተሳሰብና መከባበር እንዳይኖር ብዙ ጥረዋል:: ገዥዎቻችን በጎሳዎች መካከል የቻይናን ግድግዳ ለመቆም ከየጎሳው የመለመሏቸውን ሎሌዎቻቸውን ብቻ አልተጠቀሙም:: አሉባልታና የፈጠራ ወሬዎችን በዜጎች መካከል እየነዙ ግጭቶች እንዲፈጠሩም አድርገዋል:: ገዢዎቻችን እንኳንስ ጎሳ ከጎሳ በአንድ ጎሳ መካከል ሰንጥቀው በመግባት ደም አፋስዋል:: በዚህ ሒደት በተለይ አማራን በቁጥር ለማመንመንና አንዱን አማራ በሌላው ላይ ለማነሳሳት ብዙ ሰርተዋል:: በግፍ ተግባራቸው ለአንድ ምእተ ዓመታት በሕዝብ ጫንቃ ተጣብቀው ለመኖር ቋምጠዋል:: ግፍ እየሠሩ ግፍ ተርበዋል:: የአማራም መሬት ቀምተው ወስደዋል:: ቁጥሩንም ለማመንመን ለአስራ ሰባት አመታት በውንብድና የኖሩ በሽህዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻቸውን በአማራ ሕዝብ መሬት ላይ ወስደው አስፍረዋል:: ገዥዎቻችን ቀንቷቸዋል:: የእነርሱ ፀሀይ ጠልቃ ለሕዝብ የሚነጋበት ቀን ፈጠነም ዘገየም ሳይመጣ እንደማይቀር ለአፍታም ሳያስቡ ቀርተዋል:: እብሪት እንዲህ ያደርጋል:: ባለጌ ሥልጣን ሲይዝ ያብዳል:: እነዚህ ባንዳነትን ከአያት ቅደመ አያቶቻቸው ከጥብቅ አደራ ጋር በቅብብሎሽ ሲወርሱ የኖሩ ባንዳዎች አሁን ቢሆን የአማራን ሕዝብ በጣም ሲፈሩ ይስተዋላል:: የአማራን ሕዝብ ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ጎሳዎች ጋር በማጋጨት ተግባራቸው ቀጥለውበታል:: አሁንም ለዘመናት ከኖረበት መንደሩ በሥውር እጃቸው ሲያፈናቅሉ ይስተዋላል:: ዓላማቸውን ከመነሻውም ተናግረዋል:: ኢትዮጵያን ለማጥፋት የአማራን ሕዝብና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነትን ማዳከም እንዳለባቸው ተናግረዋል:: አገዛዙ ሐይማኖት እንደሌለውና ዓለማዊ መሆኑንም ማንም ሳይጠይቃቸው ለፍልፈዋል:: የአማራን ሕዝብ ለማዳከም ብአዴን የተባለ የእንግዴ ልጅ ጠፍጥፈው ሰርተዋል:: የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ለማዳከም ደግሞ ገብረ መድህን የተባለ ተኩላን አቡነ ጳውሎስ በሚል ቅጽል ሥም ለአምላክ ቤት አበ አበው አድርገውት በሞተ ከዳ አፈር እስኪልስ ድረስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዘረኝነትን ሲያስፋፋና ብር ሲያጋብስ እንደኖረ ይታወቃል:: ይህ በፍቅረ ንዋይ የታወረ የባንዳ ልጅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ራስ ተደርጎ በቆየባቸው ዓመታት የኣማራ ተወላጅ ጳጳሳትንና ካህናትን ቁጥር ለመቀነስ ብዙ እኩይ ተግባራትን ሰርቷል:: የአማራ ተወላጅ የሆነ መነኩሴን በእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ‹‹ቆራጥ›› ወታደራዊ ትእዛዝ በመስጠት አስረሽኗል:: ለራሱ በቁሙ ሐውልት አሳንጾ ያቆመ ከመሆኑም በላይ ሲሞት በመስታወት ሳጥን እንደተቀበረ ይታወሳል:: ይህም አንዱን የሐይማኖቱን ሥርዓት ያፋለ ድርጊት እንደነበር አንርሳ:: መነኩሴ በአሮጌ ሰኔል እንጅ እንዴት በመስታወት ሳጥን ይቀበራል? ገብረ መድህን ባለትዳርና የልጆች አባት ነበር እንዴ?

ተኩላው አገዛዝ የአገር ፍቅር ስሜትና የአርበኞች መፍለቂያ ማእከል የሆነውን የአማራ ሕዝብ በጎጥ በመከፋፈል እርስ በእርሱ ለማጋጨት ያደረገው ጥረትም ከፍተኛ እንደነበር ይታወሳል:: በተለይ የወሎንና የጎጃምን ሕዝብ ከሰሜን ሸዋ ተወላጆች ጋር ለማጋጨት በሚስጥር ሰፊ ቅስቀሳ ተደርጓል:: አንዳንዴ ደግሞ የወሎ ተወላጆችን ብቻ በመነጠል በሰሜን ሸዋ ተወላጆች ላይ ሲያነሳሳ ተስተውሏል:: ይህም ሁሉ ተደርጎ ግን የአማራ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ አቋሙ ጸንቶ ቆሟል:: ዘረኝነትን ለማስተናገድ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል:: ጎሰኝነትን ባለመቀበሉ አገዛዙ ከፍተኛ ሥነ መንግሥታዊ ኪሳራ ደርሶበታል::

ግፈኛው የጎሳ መርህ አገዛዝ ሩብ ምእተ አመት በሸፈነው አገርን በማፈራረስ ተግባሩ በተለይ የደቡብ ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ጎሳዎችን በከፍተኛ ደረጃ እርስ በእርሳቸው እንዲጋጩ አ ድጓል:: በዚህም መሠረት በ1987 ዓ.ም. ጌዲኦና ጉጅ ተዋግተው መጠኑ ቀላል ያልሆነ ሕዝብ አልቋል:: በወቅቱ የከብት ዘረፋም ተካሂዷል:: ንብረትም ወድሟል:: ጌዲኦና ጉጅ በአለፉት ሥርዓተ አስተዳደሮች ተከባብረው እንደኖሩ ይታወቃል:: የሚያጋጭ ደግሞ አንዳችም ምክንያት አልነበረም:: ከአንድነት ይልቅ ልዩነቶችን የሚያራግበው አገዛዝ ግን ኢምንት ሰበቦችን በማጉላት ሁለቱን ጎሳዎች ሊያጣላ ችሏል:: በሁለቱ መካከል የበርሊንን ግንብ ለመሥራት አስቦ የፈጸመው እኩይ ድርጊት እንደነበር ታውቋል:: ነገር ግን የአገዛዙ ዓላማ ሳይሳካ ቀርቷል:: ጌዲኦና ጉጅ ደም ቢቃባም ተመልሶ በወንድማማችነት መንፈስ ሲኖሩ ይስተዋላልና::

አገዛዙ በዚህ ብቻም አላበቃም:: በ1999 ዓ.ም. ቦረናና ጉጅን አጋጭቷል:: አገዛዙ አንዳንዴ የጎሳዎችን የንቃተ ሕሊና ማነስ መነሻ በማድረግም ያጋጫቸዋል:: ያውቅበታል፤ ይችልበታል:: ሁለቱን ጎሳዎች የሚያጋጭ በቂ ምክንያት አልነበረም:: የግፍ አገዛዝ ውጤት መሆኑን መናገሩ ብቻ በቂ ይሆናል:: በዚህ ሒደት በ2000 ዓ.ም. ደግሞ ሲዳማና አርሲ ግጭት ፈጥረው እንደነበር ታውቋል:: ምን ያክል ሕይወት እንደጠፋ ግን የታወቀ ነገር የለም:: ስለንብረት ውድመትም የተዘገበ ነገር አልሰማንም:: በተመሳሳይ መልኩ በዚሁ ዓመተ ምህረት አርሲና አላባ እንደተጋጩ ለማወቅ ተችሏል:: ቤቶች ተቃጥለዋል:: ዘረፋም ተካሂዷል:: ይህም አገዛዙ ያመጣው ችግር እንደነበር ታውቋል:: አሁንም በመቀጠል በዚሁ ዓ.ም. የኮንሶና ቦዲ ጎሳዎች ግጭት ፈጥረው ተገዳድለዋል:: ዘረፋዎችም በተከታታይ ተካሂደዋል::

ዘመኑ የውሸት ዘመን መሆኑ ይታወቃል:: እውነት ያስገድላል:: ቅጥፈት ያስከብራል:: ሐሰት ያኮራል:: ሕሊናቸውን ያልሸጡና የማይሸጡ በጣም ጥቂት ኢትዮጵያውያን በዚች አገር ላይ ስላሉ ግን እንጽናናለን:: በተመሳሳይ መልኩ በውጭ አገራትም በስደት ዓለም ለአገራችን አንድነትና ሉዓላዊነት መከበር ሌት ተቀን የሚታገሉ ጀግኖችን በታላቅ አክብሮት በአእምሯችን አስቅምጠናል:: ግን በቂ አይደለም:: የእውነተኞች ደቀ መዛሙርት መሆን አለብን:: ሕሊናቸውን በጊዜያዊ ተድላና መናኛ ጥቅም ያልሸጡ ቆራጦችን ልንከተላቸው ይገባል:: ለሕሊና መኖር ያስፈልጋል:: ጠላታችን አገዛዙ ነው:: የአገር ፍቅር ስሜት የሌላቸው፣ ከራሳቸው ጎሳ በስተቀር ሌላ ሰው የማይታያቸው፣ የዘረኝነት ሕመምተኞች፣ ስግብግቾ፣ ሌቦች፣ ውሸተኞች፣ ከፋፋዮች፣ መሰሪዎች፣ ሃይማኖት የሌላቸው፣ ይሉኝታ የማያውቁ፣ አገር ሻጮች፣ ነፍሰ ገዳዮች፣ የባንዳ ልጆች እስከ መቼ በምኒልክ አገር ላይ ሲጫወቱበት ይኖራሉ? ጥያቄው ወቅታዊና አንገብጋቢ ነው:: ደካሞች ሆነን በህዳጣን ተገዝተናል:: አገዛዙን ከነግሳንግሱ ካላስወገድን የባርነት እድሜያችን ይቀጥላል:: የግፍ አገዛዝን ከነግዛንግዙ ለማስወገድ እንታገል! እንታገል! እንታገል!

> ሕሊናቸውን በጊዜያዊ ተድላና መናኛ ጥቅም ያልሸጡ ቆራጦችን ልንከተላቸው ይገባል። ለሕሊና መኖር ያስፈልጋል። ጠላታችን አገዛዙ ነው። የአገር ፍቅር ስሜት የሌላቸው፣ ከራሳቸው ጎሳ በስተቀር ሌላ ሰው የማይታያቸው፣ የዘረኝነት ሕመምተኞች፣ ስግብግቾ፣ ሌቦች፣ ውሸተኞች፣ ከፋፋዮች፣ መሰሪዎች፣ ሃይማኖት የሌላቸው፣ ይሉኝታ የማያውቁ፣ አገር ሻጮች፣ ነፍሰ ገዳዮች፣ የባንዳ ልጆች እስከ መቼ በምኒልክ አገር ላይ ሲጫወቱበት ይኖራሉ?

# ቤንስያ

## ሲቲፒ ማተሚያ ቤት
## ከኮምፒዩተር ወደ ፕሌት (CTP)

ቤንሲያ ሲቲፒ ማተሚያ ቤት ለህትመት ስራ እጅግ ጠቃሚና በጥራቱ አስተማማኝ የሆነውን ከኮምፒውተር ወደ ፕሌት ህትመት ስራ ከጀመረ እነሆ አንድ አመት ሞላው ። በአለፉት አንድ አመታት ውስጥ ያፈራናቸ ደንበኞቻችን ለኛ ምስክሮቻችን ናቸው።

በዋነኛነት ከምንለይባቸው መካከል ጥራት ፍጥነት ቅልጥፍና ታማኝነት እና የደንበኛ አክብሮት ናቸው ከዚህም ሌላ ማሽናችን ዘመኑ የደረሰበት የቅርብ ግዜ ቴክኖሎጂ ከመሆኑም በላይ የማተም አቅሙም በሰአት እንደሚከተለው ነው።

| የፕሌት ዓይነነት | መጠን | በሰአት የማተም አቅም |
|---|---|---|
| ጂቲኦ 46 | 40 x 38 | 60 |
| ጂቲኦ 52 | 52 x 40 | 60 |
| ኤም ኦ / ኮርድ | 55 x 65 | 50 |
| ስፒድ ማስቴር 74 / ኮርስ | 76 x 62.5 | 45 |
| ስፒድ ማስቴር A1 | 1040 x 840 | 40 |

**ጥራት ቅልጥፍና ታማኝነት እና ታታሪነት የኛ መለያዎች ናቸው !**

አድራሻችን ቸርችል መንገድ ቴዎድሮስ አደባባይ (ፒያሳ)
እሸቱ ማሞ ህንፃ አንደኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 113

Tel 09 11 42 12 80
E-mail bbekele@gmail.com
bencia.printing@gmail.com



# አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ

## በሁሉም መጽሐፍት መደብር ያገኙታል

# ትግል አይቆምም



ዮሴፍ ያዘው (ሻለቃ)



# መንቶቼ የዕጽዋት (የባህል) መድኃኒት ማምረቻና መሸጫ

# MENTOCHE HERBAL MEDICINE PRODUCTION CENTER



ይህ የዕጽዋት መድኃኒት ማዕከል ሲወርድ ሲዋረድ የነበረውን የአባቶች የባህል (እጽዋት) መድኃኒት ሕክምና በማሳደግ ፍቱንነታቸዉ ተረጋግጦ በከፊል በሳይንስና ቴክኖሎጅ በማስመዝገብና ከኢንቨስትመንት ፈቃድ በመውሰድ በማምረት ላይ ይገኛል። ለዉስጥ ችግር በሚወሰድ፣ በቆዳ ላይ ለሚወጣ በመቀባት ሲሆን ከኬሚካልም ሆነ ከባዕድ ነገሮች ነጻ የሆነ ነው። ከሚመረቱት ምርቶች በከፊል

## በሚወሰድ

- ለኪንታሮት ፌስቱላ መድሀኒት በደም ዉስጥ ያለን አጥቦ የሚያወጣ ሲሆን ድርቀት፣ ወገብ ችግር፣ ጋዝና ወሲብ ችግርን ያድናል።
- ለነቀርሳ (ካንሰር) በሽታ ከደም ውስጥ አጥቦ የሚያወጣ በጭንቅላት፣ በአንገት፣ በጡትም ሆነ በአንጀት ላይ ያለዉን ያድናል።
- የደም ግፊት (ብዛት) እስከ መጨረሻዉ የሚያድን።
የኮሌስትሮል፣ የስብና የፕሮቲን ክምችትን ያቀልጣል፤ ስለሆንም ኮሌስትሮል ያጠፋል።
- ለነርቨ፣ ለሪህ፣ ለደም መወፈር (መርጋት) ለዲስክ መንሸራተት ያድናል።
- ለጉበት ሄፓታይተስ ሦስቱንም አይነት የጉበት በሽታ ያድናል።
- ለአእምሮ ጭንቀት ለሚጥል በሽታና ለሚያፈዘዉ ያድናል።
- ለቆዳ በሽታ አለርጅክም ሆነ ፈንገስ ሶራይስስ ጭምር ያድናል።
- ኤድስን የሚያባብሱ ተዛማጅ በሽታዎችን በማከም የድካም ስሜትን፣ መክሳትንና የምግብ ፍላጎት መቀነስን እንዲጨምር ያደርጋል።
- በሆድ ዉስጥ ላለ በሽታ አሜባ፣ ታይፎይድ፣ ጃርዲያ፣ አስካሪስና ውሃ ወለድ በሽታዎችን ያድናል።
- ‹‹ሸንት ለሚያስቸግረውና ለስኳ በሽታ ፍቱን መድኃኒት አለን››

## የሚቀባና በፊንጣጣ የሚገባ መድኃኒት

- ለኪንታሮት (ፊስቱላ) በሚቀባ ምንም አይነት ህመም የሌለዉ ሲሆን ሥራም የማያስፈታ ነዉ። ለቆየ የአባላዘር ለዉስጥ ኪንታሮት በፊንጠጣ የሚገባ የዉስጥን የፈንገስ ክምችት የሚያወጣ ምንም አይነት የህመም ስሜት የሌለዉ ነዉ።
- ለቆዳ በሽታ ሁሉንም አይነት ያድናል
- ያለ እድሜ ለሚመጣ የወሲብ (የብልት መፍጠን) ችግር በመቀባት የሚያድን አብዛኛዉ ሕዝብ የኪንታሮት በሽታ መድሀኒት በተመጣጣኝ ዋጋ እንሸጣለን።

**በተጨማሪም በመገናኛ ውልና ማስረጃ ፊት ለፊት ገነት ኮሜርሻል ሴንተር 2ኛ ፎቅ የመድኃኒት መሸጫና ነጻ የመርጃ ማዕከል መክፈታችን ስናበስርዎ በደስታ ነው።**
**አድራሻ፡ አዲስ አበባ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ሃና ማርያም ከጤና ጣቢያው አለፍ ብሎ**
0911 665321/ 0913 316790 / 0912 660886 / 011 4710024
ቁጥር 2፡ ሰሜን ሸዋ መሀል ሜዳ ወርልድ ቪዥን ፊት ለፊት/ ቁጥር 3፡ ጎጃም በረንዳ ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ካለበት ሕንጻ ላይ 2ኛ ፎቅ 221 ቁጥር